እንደ
# አዲስ ዘመን
ሐሙስ
81ኛ ዓመት ቁጥር 293 ሰኔ 23 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






ፎቶ ገባቦ ገብሬ

## «የዴሞክራሲ ሥርዓታችንን ለማጎልበት ሀሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግርን መታገል ይጠበቅብናል»

- ዶክተር ለገሰ ቱሉ
የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የዴሞክራሲ ሥርዓታችንን ለማጎልበት ሀሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግርን መታገል እንደሚገባ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትሩ ገለጹ። በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ የሚስተዋሉ ውጥረቶች አዲስ የዴሞክራሲ ተለምዶ የወለዳቸው መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን በተመለከተ «የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃን እየታገልን የዴሞክራሲ ሥርዓት እንገንባ» በሚል መሪ ሀሳብ ባካሄደው ውይይት ላይ እንደተናገሩት፣ ኢትዮጵያ እየተለማመደችው ባለው አዲስ የዴሞክራሲ ሥርዓት ጽንፈኝነትና አሸባሪነት ጎልቶ እየታየ ነው። በዚህ የዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ የሚስተዋለው ውጥረት «አዲሱ ተለምዶ» መሆኑን ማሳያ ነው።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ ኢትዮጵያ ከመረጃ ቴክኖሎጂ በኋላ ድህረ እውነትና አዲስ የዴሞክራሲ ልምምድ

«የዴሞክራሲ ሥርዓታችንን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ወይዘሮ መሰንበት ሽንቁጤ

ፎቶ ፡- ፀሐይ ንጉሤ

## አዲስ ቻምበር የአገሪቷን ንግድና ኢንቨስትመንት ለማጠናከር እንደሚሠራ አስታወቀ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት (አዲስ ቻምበር) የረጅም ዓመት ልምዱን በመጠቀም የአገሪቷን ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማጠናከር እንደሚሠራ አስታወቀ።

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ለሚያከናውናቸው የንግድና ኢንቨስትመንት ማጠናከሪያ ሥራዎች ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልጿል።

የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የ75ኛ ዓመት ክብረ በዓሉን አከበሯል።

በወቅቱ የንግድ ምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰንበት ሽንቁጤ፤ የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አመራርና አባላት የረጅም ዓመት ልምዳቸውን በመጠቀም የአገሪቷ ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማጠናከር አስፈላጊውን ጥረት ለማድረግ ዝግጁ ናቸው ብለዋል።

የአገሪቱን የንግድና የኢንቨስትመንት እንዲሁም

አዲስ ቻምበር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## «መልካም ነገር መሥራት ባንችል እንኳን ከክፋታችን መሰብሰብ የሁላችንም ኃላፊነት ሊሆን ይገባል»

- ኡስታዝ አቡበከር አህመድ

**ውብሸት ሰንደቁ**



አዲስ አበባ፡- መልካም ነገር መሥራት ባንችል እንኳን ክፋታችንን መሰብሰብ የሁላችንም ኃላፊነት ሊሆን ይገባል ሲሉ ኡስታዝ አቡበከር አህመድ ተናገሩ። እየተወሰደ ያለውን የሕግ ማስከበር እርምጃ ከሕዝብ ጋር በጋራ በመሥራት ዜጎች በአገራቸው ላይ ሰላምና ደህንነት ተሰምቷቸው እንዲኖሩ ማድረግ እንደሚገባም አሳስበዋል።

ኡስታዝ አቡበከር አህመድ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ዜጎች በአገራቸው ተስፋ እንዳይኖራቸውና አንገታቸውን እንዲሰብሩ ለማድረግ ፀረ ሰላም ኃይሎች በንፁሃን ዜጎች ላይ ኢሰብዓዊ ድርጊት ፈፅመዋል። ይህ እንዳይደገም እየተወሰደ ያለውን የሕግ ማስከበር እርምጃ ከሕዝብ ጋር በጋራ በመሥራት ዜጎች በአገራቸው ላይ ሰላምና ደህንነት ተሰምቷቸው እንዲኖሩ ማድረግ ይገባል።

መንግሥትም በሕግ ማስከበር እርምጃውን ጠንከር ብሎ ሊሄድበት ይገባል ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ በሕዝብ በኩልም ይህን ዓይነቱን ግፍ ከየአካባቢው ያልቀመሰ የለምና እኔ ቤት እሳቱ ስላልገባ ከሚል ስሜት በመውጣት እና በዚህ አካሄድ ሁላችንም ነገ ተረኛ ልንሆን እንደምንችል በማሰብ ከሕግ አስከባሪው ኃይልና ከፀጥታ አካሉ ጋር በመተባበር እነዚህን አሸባሪዎች ልናስወግድ ይገባል ብለዋል።

አጋጣሚውን ተጠቅሞ አገር ለመውረር የሚደረጉ ሙከራዎች እና የውስጥ ተላላኪዎች የጥፋት ሴራዎች በመኖራቸው መንግሥት በሁሉም አቅጣጫ በመወጠሩ የሚፈለገውን ነገር በሚፈለገው ፍጥነት ለማከናወን ሊቸገር እንደሚችል በመግለፅ የተፈፀመውን ድርጊት ጥፋተኛን ጥፋተኛ፤ ወንጀለኛን ወንጀለኛ ብሎ እኩል

«መልካም ነገር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በክልሉ ከ178 ሺህ ሄክታር በላይ የችግኝ መትከያ ቦታ መዘጋጀቱ ተገለጸ

ገጽ 3






# የጥቁር አንበሳ ጥቁር ነጥቦች

**ዳግማዊት ግርማ**




ደስታና ኀዘን ጤናና ህመም ማጣትና ማግኘት ብቻ ብዙ ተቃራኒ ግን መንታ የሆኑ በሰው ልጅ የመኖር ሂደት ውስጥ የሚታቀፉ የሕይወት ሕግጋት ናቸው። በመኖር ብዙ ቢታይም በሕይወት እልፍ ቢደመጥም ዛሬ ግን ለሰው ልጅ የህመም ድህነት መገኛ ተብሎ ስለተቋቋመው የህክምና ተቋም ጥቁር ነጥቦች እናውጋ።

በብዙ መከራ ውስጥ አልፈው ነገን ለማየት ብዙ መሥራት በሚጠበቅባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገራት ውስጥ የመንግሥትም ሆኑ የግል የህክምና ተቋማት የዜጎችን ጤንነት ከማስጠበቅ አኳያ ብዙ ሥራዎች ይጠበቅባቸዋል። ይህን እውነታ ለመታዘብና የህሙማን አያያዝ ለመቃኘት በመንግሥትና ሕዝብ ባለቤትነት ስር ስለሚንቀሳቀሰው እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስር በሚተዳደረው በዕድሜም በስፋትም ወደ ገዘፈው ዕድሜ ጠገቡ የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ቅጥር ግቢ ተገኘን።

በግቢው ብዙ ዓይነት ባህሪና ቁመና ያላቸው ሰዎች እዚህም እዚያም ወደየጉዳዮቻቸው ይመላለሳሉ። የማን ማረፊያ የት እንደሆነ ባይታወቅም ሁሉም ተጓዥ ነው። ከህመሙ አገግሞ ለቤት ለዘመዱ ከሚበቃ ጀምሮ በእግሩ መጥቶ አስከሬኑ እስከሚወጣው ድረስ ሁሉም ፊት ላይ የጭንቀት ስሜት ማንበብ የተለመደ ነው። በአጭሩ በግቢው ውስጥ ታማሚ አስታማሚ አካሚና የሆስፒታሉ የትኛውም ጫፍ ላይ በመሥራት የሚተዳደር የሰው ጎርፍ ይፈሳል።

ታማሚው ብዙ ዓይነት ነው፤ ልቡ ከአልጋ በጣለው ደዌ የተጎዳ፣ ነፍሱ ህቅ ልትል የሚቃትት፣ ከሞት ቅፅበት አዳኞችን የሚጠባበቅ፣ ከሀኪም የትሞታለህ ተስፋ አስቆራጭ ቃል ያደመጠ፣ በይሆን ይሆን ተስፋ ከህመሙ በላይ ተስፋ ማድረግ ያደከመው፣ ህመሙን የሚረዳ፣ ወጥቶ ወርዶ የሚደግፈው አስታማሚ ዘመድ ወገን ያጣ፣ ህመሙን በብቸኛ ነፍሱ ታቅፎ የሚሄድ፣ በሽታው ከመድኃኒቱ ያልተገናኘለት ብቻ ታማሚ እልፍ ዓይነት ነው።

አስታማሚውም እንደ ታካሚው ብዙ ዓይነት ነው፤ በህመም የዛለ ዘመድ አዝማዱን በይተርፍልኛል ተስፋ በቢድንልኝ ፀሎት ለሰማይኛው አንጋጦ አቤቱታውን የሚያቀርብ፤ ማስታመም ያሳመመው፣ ጉልበቱ በሆስፒታሉ ቀዝቃዛ የብረት ወንበሮች ምክንያት የዛለ፣ አንድና ብቸኛ ዘመዱን ህመም ጎድቶበት የብቸኝነት ህመም ቤቱን እያንኳኳበት የሚገኝ ጭምር ነው።

አካሚውም ብዙ ዓይነት ነው፤ ለሰው ነፍስ መትረፍ የሚከፍለውን ለመክፈል ቆርጦ የተነሳ እንስፍስፍ ልብ ያለው፣ ከሥራ ውጪ ለሚሠራበት የግል ድርጅት የሚከፈለውን ክፍያ እያሰበ በሆስፒታሉ ግማሽ አካሉ ብቻ ያለ፣ ሌላም ሌላም።

ወደ አንዲት እናት ጠጋ ብለን ያሉበትን ሁኔታ ለማጥናት ሞከርን። በዕድሜያቸው ገፋ ያሉ እናት ናቸው፤ ልጃቸው ከጤና ጣቢያ «ሪፈር» ተብላ ልትወልድ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል መገኘታቸውን ይገልፃሉ። ልጃቸው ዘጠኝ ወራት ከአስራ አምስት ቀን ሆኗታል።

አዛውንቷ እርጉዝ ልጃቸው በሰላም ተገላግላ የአያትነትን ወግ ያሳየቻቸው ልጃቸው ይህንኑ ጸጋ ደግማ እንድታጎናፅፋቸው ይሻሉ።

በሆስፒታሉ የሚገኙ ሀኪሞች የልጃቸው ፅንስ መገልበጡንና እናትየውም ልጅም አደጋ ላይ በመሆናቸው እንዳትወጡ ብለዋቸው እናትየው ቀዶ ጥገና እንደሚያስፈልጋት ነግረዋቸው በመጠባበቅ ላይ እንዳሉ ገልፀው፤ ትናንት ልጃቸውን በመከታተል ላይ የነበረው ሀኪም አንድ መጥፎ ነገር እንዳይፈጠር እናቲቱ ለሰከንድ ለመዘዋወር እንኳ ከሆስፒታሉ አይን መራቅ አይገባሽም ብለዋት እንደነበር ያወሳሉ።

በማግስቱ ደግሞ ያ ሁሉ ችግር ተወርቶና የእናትየውም የፅንሱም ሕይወት አደጋ ላይ ባለበት ሁኔታ ሌላኛው ተረኛ ዶክተር ክፍሉን ለቀው እንዲወጡ እንደጠየቃቸውና ማንን እንዴት ማናገር እንዳለባቸው እንኳ ግራ መጋባታቸውንም በኀዘን ተሞልተው አውርተውናል።

ሁለተኛ ቅሬታ አቅራቢያችን አበራሽ ናት(ስሟ የተቀየረ)። በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥ በህመም የሚማቅቁ ባለቤቷን ልታስታምም መጥታ ወደ ቤቷ ለመመለስ ትራንስፖርት በመጠበቅ ባለችበት ወቅት ነው የተገናኘነው። የወጣትነት ዕድሜዋን ችግር የፈጀባት የምትመስል አሁናዊ ዕድሜዋ በጎልማሳነት ዘመን ውስጥ ያለች መልከመልካም ናት፤ በሆስፒታሉ አሠራር ተማራ አወጋችን። የምታስታምማቸው የሽንት ቧንቧቸውን የታመሙ አባት ናቸው፤ በሰው ሰራሽ መሸኛ ነው የሚጠቀሙት።

ለረጅም ጊዜያት ከሰበታ ወደ ሆስፒታሉ መመላለሷን የነገረችን አስታማሚዋ፤ ያለምንም ህክምና ለቀጣይ ሳምንት መቀጠሯን ገልፃልናለች። ከሥራው ሩቅነት ከህመሙ ፅናት የተነሳ በሆስፒታሉ አገልግሎት አሰጣጥ በብዙ ማዘኗንም ነግረናለች።

ሦስተኛው ስሞታ አቅራቢያችን አቶ አዳሙ(ስማቸው የተቀየረ)፤ ወንድማቸውን ለማሳከም ከጎጃም ነው የመጡት። ከበሽታው ከባድ ባህሪ በላይ ብዙ ነገሮች አሰቃይቷቸዋል። የካንሰር ህክምናን በሚመለከት በህሙማን አልጋና አገልግሎት አሰጣጥ ችግር እየተጉላላን ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በታማሚና አስታማሚ ለቀረቡለት ስሞታዎች ምላሽ ስጡኝ ለማለት የጥቁር አንበሳ ሆስፒታልን በር ያለመታከት ለቀናት በተደጋጋሚ አንኳኩቶ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ቺፍ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተሩን ዶክተር አንዷለም ደነቀን አነጋግሯል።

ዶክተር አንዷለም ከአምስት መቶ ሺህ በላይ ሕዝብን በሚያስተዳድረው የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ካለው የሕዝብ ብዛት አንፃር ችግሮች አይኖሩም አንልም፤ እንደየአመጣጣቸው ግን ለመፍታት ጥረት እናደርጋለን ብለዋል። ለዶክተር አንዷለም ችግሮቹ የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በካንሰር ህክምና ዘርፍ ብቸኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚመጡ እጥረቶች በመኖራቸው አልጋ ማጠር ካለው የህመምተኛ ቁጥር አንፃር የሚጠበቅ መሆኑን ገልፀዋል።

እንደዶክተር አንዷለም እይታ ሀኪምና ቅሬታ አቅራቢዎቹን ፊት ለፊት ማገናኘት ካልተቻለ በቀር ከወላዲቷ ጋርና ከሽንት መሸኛ ቱቦ አንፃር የተነሱት ቅሬታዎች ተጨማሪ ማብራሪያን ይሻሉ፤ ትክክለኛ ምክንያትና ችግሩን ለይቶ ማውጣት እንደሚከብድ እንዲሁም የሀኪሙንም የህመምተኛውንም ቃል መውሰድ ከባድ መሆኑንም ገልፀዋል።

ለዶክተር አንዷለም ሀኪሙ ራሱ የሚቆረቆርለት ሰው ያስፈልገዋል፤ አንድ ዶክተር እስከ ሰላሳ ስድስት ሰዓት ያለማቋረጥ ይሠራል። በዚህ ውስጥ የሚፈጠሩ ስህተቶች አይጠፉም። ህክምና ታማሚዎችም ምንም ዓይነት ቅሬታ ካላቸው ከሆስፒታሉ ሳይወጡ ማጋለጥ እንደሚችሉ በመጠቆም እርሳቸው እንኳን በግላቸው በቀን ቢያንስ አስር ታካሚዎችን የማየት ዕድል እንዳላቸውም ገልጸዋል።

ዶክተር አንዷለም ሆስፒታሉ የተገልጋዮቹን ፍላጎት ለማርካት በርካታ ሥራዎችን በመስራት ላይ እንደሚገኝና የማህበረሰብ መድኃኒት ቤት በመክፈት እንዲሁም የሆስፒታሉን ቅጥር የማደስ ሥራን በመከወን ማህበረሰቡን ለመጥቀም በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝም አመላክተዋል።

# የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እንደሚሰጥ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እንደሚሰጥ የትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ።

የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በሆሳዕና፣ በወራቤና በወልቂጤ ከተሞች የሚገኙ ሁለተኛ ደረጃና ሞዴል ትምህርት ቤቶችን በጎበኙበት ወቅት ከተማሪዎችና ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር ባደረጉት ቆይታ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና በትምህርት ቤቶች ሳይሆን በዩኒቨርሲቲ ውስጥ እንደሚሰጥ ገልጸዋል።

እንደሚኒስትሩ ገለጻ፤ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና በኦንላይን መስጠት እስከሚጀመር ድረስ በዩኒቨርሲቲዎች መሰጠቱ ይቀጥላል።

የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና በዩኒቨርሲቲ እንዲሰጥ የተወሰነው የፈተና ሰርቆትና ማጭበርበርን ለማስቀረት ታስቦ በመሆኑ ተማሪዎች ትምህርት በሥራና በታታሪነት የሚገኝ መሆኑን አውቀው በርትተው መማርና ማጥናት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

የትምህርት ሚኒስቴር የትምህርትን ጥራትን ለማሻሻል በአጠቃላይና ከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፎች ሌሎችንም የተለያዩ እርምጃዎች በመውሰድ ላይ መሆኑንም ፕሮፌሰር ብርሃኑ ጠቁመዋል ሲል የዘገበው ኤፍቢሲ ነው።



ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ

# በክልሉ ከ178 ሺህ ሄክታር በላይ የችግኝ መትከያ ቦታ መዘጋጀቱ ተገለጸ

**ሙሳ ሙሐመድ**





አዲስ አበባ፡- ለ2014ዓ.ም የአረንጓዴ አሻራ ማኖር መርሃ-ግብር የችግኝ መትከያ የሚውል ከ178 ሺህ ሄክታር በላይ ቦታ ተለይቶ ማዘጋጀቱን የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

የክልሉ ግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ዳይሬክተር አቶ እስመለዓለም ምህረቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ በክልሉ በዘንድሮ አመት የአረንጓዴ አሻራ ማኖር የሚውል ከ178 ሺህ ሄክታር በላይ የችግኝ መትከያ ቦታ ተለይቶ ተዘጋጅቷል።

እንደ አቶ እስመለዓለም፣ ለችግኝ መትከያ በተለዩት አብዛኛው አካባቢዎችም የችግኝ መትከያ ጉድጓድ ቁፋሮ ተደርጓል።

በክልሉ የዘንድሮው አረንጓዴ አሻራ ማኖር አንድ ነጥብ 42 ቢሊዮን በላይ የተለያዩ ዝርያዎች ያሏቸው ችግኞች ተፈልተው ለተከላ ተዘጋጅተዋል ያሉት አቶ እስመለዓለም፣ ከተዘጋጀው ውስጥ 250 ሚሊዮን የሚሆነውን በሁሉም ዞኖች ሐምሌ ስድስት ላይ በአንድ ጀምበር ለመትከል ታስቧል ብለዋል።

አሳታፊውና በሁሉም ዞኖች የሚደረገው የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላም በዝናቡ የመጠናከርና የመቆራረጥ ሁኔታ ቀኑ ሊራዘም እንደሚችልም አቶ እስመለዓለም ተናግረዋል።

እንደ ክልል የተከላ ሥራውን በመተባበር ተፈልቶ ለተከላ ዝግጁ የሆኑትን ከአንድ ነጥብ 42 ቢሊዮን በላይ ችግኞች መትከል ይጠበቀብናል ብለዋል።

የአረንጓዴ አሻራን ማኖር በክልሉ ሰኔ 17 ቀን በጎንደር ከተማ አስተዳደር ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ ያሉ ከፍተኛ አመራሮች፣ የግብርና ዘርፍ አመራሮች በተገኙበት በይፋ መጀመሩን ያወሱት ዳይሬክተሩ፣ በተለይ ኅብረተሰቡን በማሳተፍ በተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ ጥበቃና በአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ በተሠራው ሥራ እስከ አሁን 13 ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ችግኝ ተተክሏል። የተተከሉት ችግኞችም አገር በቀልና የፍራፍሬ ዝርያዎች ናቸው ብለዋል ዳይሬክተሩ።

ከ2014 ዓ.ም የአረንጓዴ አሻራ ማኖር ከተዘጋጀው ቦታ በተጨማሪም በክልሉም ለደን ልማት ሊውሉ የሚችሉ 31 ሺህ 110 ሄክታር በላይ መሬት ካርታ ከተሰርላቸው በያዝነው ዓመት ለአረንጓዴ አሻራ ልማት አገልግሎት ይውላሉ ብለዋል።

አቶ እስመለዓለም አያይዘውም በመላው አገራችን የመንግሥትም ይሁን የግል ተቋማት በአላቸው የቅጥር ግቢ ቦታ ስፋት ልክ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የተለያዩ ችግኞችን በመትከል ደኖችን በማልማት፣ በመንከባከብ አካባቢያቸውን መጠበቅ ይገባቸዋል ብለዋል።

ጽድቀትን በተመለከተ ልዩ ትኩረት እንደሚሰጥ የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፤ ከዚሁ ጋር አያይዘውም የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላው ከተጀመረበት ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በየአመቱ የጽድቀት ምጣኔው እያደገ በ2013 ዓ.ም 84 በመቶ መድረሱን አብራርተዋል።

የክልሉ ግብርና ቤተሰብና ባለሙያዎችም በቀን ሦስት ችግኝ ለ30 ቀናት የመትከል ሥራም የመርሃ-ግብሩም አንድ አካል መደረጉንና ባለሙያዎች በወር 90 ችግኞችን እንዲተክሉ መደረጉን አመላክተዋል።



# የማኅበረሰቡን የልማት ጥያቄዎች በመመለስ ብልጽግናን ለማረጋገጥ እየተሠራ መሆኑን ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የክልሉ መንግሥት የማኅበረሰቡን የልማት ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ በመመለስ ብልጽግናን በተግባር ለማረጋገጥ እየሠራ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ አስታወቁ።

ርዕሰ መስተዳድሩ በባሌ ዞን ሮቤ ከተማ በተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች ድጋፍና በመንግሥት በጀት የተሠሩ ፕሮጀክቶችን ትናንት ሲመርቁ እንደገለጹት፤ የክልሉ መንግሥት የሚሰበሰበውን ገቢ በመጨመር የፕሮጀክት ግንባታ አፈጻጸም ደረጃን እንዲጨምር እያደረገ ነው። ከመንግሥት በጀት በተጨማሪም በበጎ ፍቃድ አገልግሎትና በልማት ድርጅቶች ድጋፍ በርካታ ፕሮጀክቶች መገንባት ተችሏል።

በክልሉ ባለፈው ዓመት በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ከ3ሺህ የሚበልጡ የቡኡረ ቦሩ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች መገንባታቸው ለአብነት ጠቅሰዋል።

አቶ ሽመልስ እንዳሉት፣ በክልሉ በተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች ድጋፍ የተሠሩትን ጨምሮ ከአንድ ሺህ የሚበልጡ የልማት ፕሮጀክቶች በልማት ድርጅቶችና በመንግሥት በጀት መገንባታቸውንም አመልክተዋል።

በሮቤ ከተማ ትናንት የተመረቁት ትምህርት ቤቶችና የእናቶችና ሕፃናት ህክምና ማዕከላት የዚሁ አካል እንደሆኑ አመልክተዋል።

በተለይ በተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች የበጀት ድጋፍ የተሠሩ ፕሮጀክቶች የሁለቱን አገራት የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ይበልጥ የሚያጠናክሩ በመሆኑ አመስግነዋል።

የተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች የዓለም አቀፍ ቀይ ጨረቃ ፀሐፊ ሚስተር ፈሃድ አብዱረህማን ቢን ሱልጣን በበኩላቸው አገራቸው በኢትዮጵያ ወንድማማችነትና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን የሚያጠናክሩ የልማት ፕሮጀክቶችን በመሥራት ድጋፏን እንደምትቀጥል አስታውቀዋል።

«ኢትዮጵያ አሁን ላይ ትክክለኛ የእድገት ጎዳና ላይ ትገኛለች» ያሉት ሚስተር ፈሃድ፣ «ኢትዮጵያውያን የተጀመረውን ልማት በማስቀጠል አገራቸውን ማሻገር አለባቸው» ሲሉ አስገንዝበዋል።

በሮቤ ከተማ ከ300 ሚሊዮን ብር በላይ የተገነቡ የጀነራል ዋቆ ጉቱ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፣ የእናቶችና ሕፃናት የህክምና ማዕከል፣ የባሌ ዞን አስተዳደር ሕንፃንና የጀነራል ዋቆ ጉቱ መታሰቢያ ሐውልት ትናንት በፕሬዚዳንት ሽመልስ አብዲሳ ተመርቀዋል።

# ተቋርጦ የነበረው የድጋፍ ሰጪ አውቶቡሶች አገልግሎት ዳግም ተጀመረ

**ሙሳ ሙሐመድ**




አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ለቀናት ተቋርጦ የነበረው የሸገር ትራንስፖርት ድጋፍ ሰጪ አውቶቡሶች ከሰኔ 22 ጀምሮ አገልግሎቱን መቀጠላቸውን የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር እፀገነት አበበ እንደተናገሩት፣ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎትን ሲሰጡ የነበሩት የሸገር ትራንስፖርት ድጋፍ ሰጪ አውቶቡሶች ከሰኔ 18 ጀምሮ አገልግሎት መስጠት አቋርጠው ነበር። ችግሩን ለመፍታት በተደረገው ስምምነት አቋርጠውት የነበረውን የትራንስፖርት አገልግሎት ከትናንት ሰኔ 22 ቀን ጀምሮ መስጠት ቀጥለዋል።

እንደ ዳይሬክተሯ ገለጻ፤ የድጋፍ ሰጪ አውቶቡሶቹ አገልግሎት ያቋረጡት ውል ባለማደስ፣ በአገልግሎት ክፍያ መዘግየትና የይሻሻልልን ጥያቄ፣ የነዳጅና የመለዋወጫ ዕቃዎች መጥፋት እንዲሁም ከትራንስፖርት ዋጋ ታሪፍ ጋር አለመስማማት በመፈጠሩ የተነሳ ነበር።

ችግሩን ለመፍታት በተደረገው ውይይት የድጋፍ ሰጪ አውቶቡስ ባለቤቶችና ማህበራቱ ጥያቄያቸው ተመልሶ ወደሥራ ገብተዋል ሲሉ አስረድተዋል።

የድጋፍ ሰጪ አውቶቡሶችን የውል ይራዘም ጥያቄ በመመለስ ውላቸው ለስድስት ወራት ተራዝሟል። ወርሃዊ የአገልግሎት ክፍያቸውም እንዲሻሻል ተደርጓል ብለዋል።

የከተማ አስተዳደሩና የአውቶቡሶቹ ማህበር ከሸገር የብዙኃን ትንስፖርት ቢሮ ጋር ባደረጉት ንግግር በቀጣይም መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች እንደሚስተካከሉና የዘገዩ የአገልግሎት ክፍያዎች በአጭር ቀናት እንደሚፈጸሙ መግባባት ላይ ተደርሷል ሲሉ ዳይሬክተሯ ተናግረዋል።

በከተማዋ የትራንስፖርት እጦትና በክረምቱም ሊከሰት የሚችለውን ችግር ለመቅረፍ 640 መደበኛ አውቶቡሶችን ወደ ሥራ ለማስገባት ታቅዶ እንደነበር የገለጹት የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተሯ፤ በተለያዩ ምክንያቶች ከታሰበው በታች 505 አውቶቡሶች ዝግጁ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በተመሳሳይም ሸገር የተማሪዎች አውቶቡስን ሳይጨምር በክረምቱ ወቅት ወደሥራ ለማስገባት 223 የሸገር አውቶቡሶችን ለማስገባት ታቅዶ 201 አውቶቡሶች ለአገልግሎት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል።በተጨማሪም 505 የአንበሳ አውቶቡሶችም የሕዝብ ትራንስፖርት እንደሚሰጡ አስታውቀዋል።

በሌላ በኩል በመዲናዋ ያለውን የትራንስፖርት ችግር ለመቅረፍ ቆመው የነበሩ የአልያንስ አውቡሶችን ወደ ሥራ ለማስገባት ቢሮው እየተነጋገረ መሆኑን የገለጹት ዳይሬክተሯ፤ 25ቱን ወደ ሥራ መግባታቸውን ጠቁመዋል።

በመዲናዋ ያለውን የትራንስፖርት አገልግሎት ችግር ለማቃለል የልዩ አገልግሎት ሰጪ አውቶቡሶችን ወደሥራ ለማስገባት ከተለያዩ የአገር አቋራጭ አውቶቡስ ባለንብረቶች ጋር ውይይት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

በተለያዩ አካባቢዎቹ የሚገኝ ኅብረተሰብ በተደጋጋሚ የሚያቀርባቸውን የትራንስፖርት አቅርቦት ቅሬታዎችን መሠረት በማድረግ ችግሩን ለመፍታት የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን አስታውቋል።

# «መልካም ነገር...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

በማውገዝ ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባ ገልፀዋል።

እንኳን እንደዚህ በርካታ ቁጥር ያለው ኢሰብዓዊ ጭፍጨፋ ይቅርና የአንድም ንፁህ ነፍስ ቢሆን ተግባሩ አስነዋሪ ነው ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ ይህ እየተደጋገመ ያለ ነገር ስለሆነ ተረባርበን ችግሩ እስከመጨረሻው ድረስ እልባት እንዲያገኝ እና ዜጎች የትም ቦታ ተንቀሳቅሰው ሠርተው መብላት የሚችሉበት ነፃነት አግኝተው መኖር እንዲችሉ ማስቻል ይኖርብናልም ብለዋል።

ምጥ ላይ ያለች አገር እንደመሆኗ እንደ አገር እያለፍናቸው ካሉ ፈተናዎች አንዱ ይህ እንደሆነ የገለፁት ኡስታዝ አቡበከር፤ በዚህ ሦስት እና አራት የለውጥ አመታት ውስጥ ሁሉም በየአቅጣጫው የራሱን የበላይነት ለማስጠበቅ፤ የራሱን ሥምና የፖለቲካ ሃሳብ ለማራመድ እና ለመጫን የተለያዩ ነገሮችን ሲጠቀም እየተስተዋለ እንደሆነ አብራርተዋል። ሆኖም ይህ የከፋ የሚሆነውና ልብን የሚሰብረው ደግሞ በንፁሐን ዜጎች ሕይወት ላይ ለፖለቲካ ትርፍ ተብሎ የሚደረግ ሲሆን እንደሆነ ተናግረዋል።

ኡስታዝ አቡበከር ሰዎች በሌሎች አገራት ተዘዋውረው እየሠሩ ባለበት ዓለም በአገራቸው እንዲህ ዓይነት አሰቃቂ ተግባር ሲፈፀምባቸው የፈፃሚዎቹን ከሰብዓዊነት በታች የዘቀጠ ስብዕና እንደሚያሳይ ጠቁመው፤ ምንም ዓይነት የፖለቲካ ተሳትፎ በሌላቸውና ጦር መሣሪያ ባልታጠቁ ንፁሃን ዜጎች በማንነታቸው እንዲህ ዓይነት ጭፍጨፋ ሊደረግባቸው አይገባም ሲሉ ገልፀዋል።

እንደ ኡስታዝ አቡበከር ገለፃ፤ ለምንም ዓይነት የፖለቲካ ሃሳብ፣ ፍላጎት ወይም የሌላ ዓላማ ማስፈፀሚያ ሲባል ንፁሃንን የዕርድ ከብት አድርጎ እና መስዋዕት አድርጎ መጠቀም ከሰብዓዊነት ውጪ ነው። በተለይ ደግሞ መስዋዕት የተደረገው ሰው ጋር በአንድ አገር ነዋሪ እና ለዘመናት አብሮ የኖረ ወንድም ሆኖ ሲገኝ ድርጊቱ ከዚያ በላይ ይሆናል። በመሆኑም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሊያወግዘውና ሊቃወመው የሚገባና እስከመጨረሻው ድረስ ይህ ጉዳይ እንዳይደገም ሁላችንም እጅ ለእጅ ተያይዘን ልንቋጨው የሚገባ ነው።

ሰዎች በዚህን ያህል ቁጥር ተገድለው ሲቀበሩ፤ ሰው በማንነቱ ተመርጦ ይህ ሁሉ ፈተና ሲደርስበት ሞትን ያህል ነገር በዚህ ያህል ቁጥር ለመድነው ወይ የሚለው ነገር ያስፈራኛል ያሉት ዑስታዝ አቡበከር፤ አገር ውስጥ ያለውን ሰላም ለማናጋት፤ እርስ በርስ ያለውን መከባበርና አብሮነት ለማደፍረስና ለማጥፋት ይህ ሁሉ ሆኗል፤ ከዚህ በላይ ግን እንደ አገር ሊበቃን ይገባል ብለዋል።

መልካም ነገር መሥራት ባንችል እንኳን ክፋታችንን መሰብሰብ የሁላችንም ኃላፊነት ሊሆን እንደሚገባ ገልፀው፤ ዜጎች ለሰላም የራሳቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ አሳስበዋል። በማህበራዊ ሚዲያ ያላግባብ የተሳሳ መረጃ በመስጠት እምነትን፣ ብሔርንና ሌሎችን መገለጫዎች ተጠቅሞ አንዱን በሌላው ላይ በማነሳሳት በሰው ደም የሚነግዱ አካላት ለጥቅም መገዛታቸውን እና በሰው ሕይወት ላይ ቁማር መጫወታቸውን ሊያቆሙ ይገባልም ብለዋል።

ይህች አገር የጋራ አገራችን እንደመሆኗ የሁላችንን ጥረት ትፈልጋለች ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ በዚህ ሁኔታ ሁሉም የራሱን አስተዋፅዖ ማበርከት ካልቻለ ዋጋ የምንከፍለውም ሆነ የምንጠፋው አብረን ነው ሲሉ አሳስበዋል። የእያንዳንዳችን ማንነት ልንተዋወቅበትና ልንረዳዳበት የተሰጠን እንጂ ልንጠፋፋበት የተሰጠን አይደለም። ይህንን መሠረት አድርገን መከባበር፣ መተባበር እና ዕውቅና መሰጣጠት ይኖርብናል። ይህን ማድረግ ካልቻልን ፈተናው የሁላችንም፤ መከራውም የሁላችንም ይሆናልም ሲሉ አብራርተዋል።

ከተከሰተው በላይ ደም ፈሶ ላለማየት ቃል መግባት እንደሚያስፈልግ ኡስታዝ አቡበከር ተናግረው፤ የተጎዱ ዜጎችን ለማፅናናትና ሕይወታቸውን ወደ ቀድሞው ለመመለስ ከጎናቸው መቆም ይገባል ሲሉ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

ከሰሞኑ አሸባሪውና ፅንፈኛው የሸኔ ታጣቂ ቡድን በምዕራብ ወለጋ በንፁሃን ዜጎች ላይ በተለይም በሴቶችና ሕፃናት ላይ አሰቃቂ ጭፍጨፋ ማድረጉ የሚታወስ ነው።

# ባለፉት ዓመታት ሴቶችን በአገር ጉዳይ ንቁ ተሳታፊ ለማድረግ የተሠራው ሥራ ውጤት እያመጣ ነው

## - የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት

አዲስ አበባ፡- ሴቶችን ተጠቃሚ እና በአገር ጉዳይ ንቁ ተሳታፊ ለማድረግ የተሠራው ሥራ ውጤት እያመጣ መሆኑን የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ ተናገሩ።

የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አንደኛ ጉባኤ «የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለሁለንተናዊ ብልጽግና» በሚል መሪ ሀሳብ በሐዋሳ ከተማ በመካሄድ ላይ ነው።

የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ በጉባኤው ላይ ባደረጉት ንግግር፣ ባለፉት ዓመታት ሴቶችን በአገር ጉዳይ ንቁ ተሳታፊ፣ ተጠቃሚና ባለቤት ለማድረግ የተሠራው ሥራ ውጤት እያመጣ ነው ብለዋል።

የሴቶችን ብልፅግና ለማረጋገጥ ለሴቶች ብድር በማመቻቸት እና የራሳቸውን ሀብት አፍርተው በአገር ኢኮኖሚ የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ለማስቻል በርካታ ተግባራት መከናወናቸውንም ገልጸዋል።

አቶ አደም ፋራህ እንዳሉት፤ የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መልካም ጅምሮች ቢኖሩም ብዙ የሚቀሩ



አቶ አደም ፋራህ

ሥራዎች አሉ። ሴቶችን በአገር ጉዳይ ቀዳሚና እኩል ተሳታፊ ለማድረግ እንዲሁም ውሳኔ ሰጪ እንዲሆኑ ለማስቻል ፓርቲው ጠንክሮ ይሠራል።

በቅርቡ በወለጋ የተከሰተውን ጭፍጨፋ በተመለከተም አካባቢው አሁን ወደ ሰላም እየተመለሰ መምጣቱን ጠቁመው፣ መንግሥት ሕግን በማስከበር የዜጎችን ሰላም ለማረጋገጥ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ማኅበረሰቡም የራሱን አካባቢ ሰላም በመጠበቅ የአገሩን ሰላም ማረጋገጥ እንዳለበትም አመልክተዋል።

የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ እንደገለጹት፤ ሴቶች በአገር ጉዳይ ላይ ተሳታፊ ከመሆን በተጨማሪ የውሳኔ ሰጪነት ደረጃ ላይ ተቀምጠዋል። በተቀመጡበት የኃላፊነት ቦታ ውጤታማ በመሆን አቅማቸውንም አሳይተዋል።

የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሠረት መስቀሌ በበኩላቸው፤ ሴት የብልፅግና ፓርቲ አባላትን ቁጥር ወደ 2 ሚሊዮን ማድረስ መቻሉን ገልጸው፣ የትውልድ ግንባታን በማጠናከር የአገርን ሰላምና አንድነት ማስጠበቅ ላይ በትኩረት መሥራት ይገባል ብለዋል።

የፖለቲካ ቁማተኞች የሚያደርጉትን እኩይ ተግባር መታገል እንደሚገባም አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

# «የዴሞክራሲ ሥርዓታችንን...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

እያደረገች ትገኛለች። በዚህም ሁኔታ እንደ ፖለቲከኛ፣ አክቲቪስትና ማህበራዊ ሚዲያ ያሉ የተከፋፈሉ ኃይሎች ተፈጥረዋል። ይህ ለአገሪቷ አዲሱ ተለምዶ ሲሆን፣ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችና ውጥረቶችም በአዲሱ የዴሞክራሲ ሥርዓት የተፈጠሩ ናቸው።

በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ውጥረት መኖሩ አዲሱ ተለምዶ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ዴሞክራሲያዊ ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ እነዚህ እውነታዎች የሉም በማለት በዚህ የልበ ሰፊነት የዴሞክራሲ ልምምድ ውስጥ ሀሰተኛ መረጃዎች መስፋፋት መቻላቸውን ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃዎች ስርጭት ለፖለቲካ አለመረጋጋት፣ ለአገራዊ አንድነትና ለሰብዓዊ ክብር ጠንቅ በመሆናቸው፤ የሀሰት መረጃንና ጥላቻ ንግግር የሚያሰራጩትን መቆጣጠር እንደሚገባም አስረድተዋል።

የቴክኖሎጂ እድገቱ ትክክለኛ መረጃ ከማግኘት ይልቅ ስሜት ኮርኳሪና ሀሰተኛ መርጃዎች እንዲበዙ ማደረጉን ሚኒስትሩ ተናግረዋል። ይህንን በመታገልና የመረጃዎችን እውነትነት በመመርመር ጠንካራ አገር መፍጠር እንደሚገባ ገልጸዋል። ሀሰተኛ መረጃና ጥላቻ ንግግርን ለመታገል የኅብረተሰቡን ንቃተ ህሊና ማሳደግ ዋነኛ መፍትሄ መሆኑንም አመልክተዋል።

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ መሀመድ እድሪስ በበኩላቸው፣ የአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲጎለብት የሀሳብ ነፃነት ከፍተኛ ሚና እንዳለው ጠቁመዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሀሰተኛ መረጃና ጥላቻ ንግግር እየተስተዋለ እንደሚገኝና ለዚህ ደግሞ የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ምክክር እየተደረገበት እንዳለ ጠቅሰዋል።

በኢትዮጵያ እየተስተዋለ ያለው የሀሰተኛ መረጃና ጥላቻ ንግግር ስርጭት እየሰፋና በሕዝብ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ መሆኑን ገልጸዋል። ይህም የመረጃ አካላት ትክክለኛውን መረጃ በወቅቱ ባለማድረስ እንደሚፈጠርና በአገር ግንባታ ሂደት ውስጥ እንቅፋት እየሆነ መምጣቱን አመልክተዋል።

ሀሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግር የአገር ግንባታን ሊፈትን ስለሚችል ችግሩን ለመግታት የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎችን ለኅብረተሰቡ ማስገንዘብ እንዲሁም ተጠያቂነትን ማስፈን ላይ በትኩረት መስራት እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል።

# አዲስ ቻምበር...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

አጠቃላይ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች እየተከታተሉ የፖሊሲና ሌሎች ምክረሃሳቦችን ለመንግሥት በማቅረብ ቻምበሩ ኃላፊነቱን በተግባር እያሳየ መምጣቱን የተናገሩት ወይዘሮ መሰንበት፤ በቀጣይም የንግዱ ማኅበረሰብ ዕውነተኛ ድምጽ ሆኖ ችግሮችን ለመቅረፍ ሙያዊ ጥረት እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት 75ኛ ዓመት ምስረታውን ሲያከብር ለመጪው ዘመን የሰነቀውን ተስፋ የሚያመላክትበትና የንግዱ ማኅበረሰብ እንደራሴነት ቃልኪዳኑን የሚያድስበት ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል።

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሃሰን መሐመድ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ያለውን ልምድና የዘመናት ተሞክሮ በመጠቀም ለሚያከናውናቸው የንግድና ኢንቨስትመንት ማጠናከሪያ ሥራዎች ሚኒስቴሩ ድጋፍ ያደርጋል።

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከተመሠረተ ጊዜ ጀምሮ በአገሪቱ የንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ ሚና ያለውን የንግድ



አቶ ሃሰን መሐመድ

ማኅበረሰብ ተወካይ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በቀጣይም የንግዱን ማኅበረሰብ ጥራት ያላቸውን ምርቶች እንዲያቀርብ በመደገፍ ረገድ ያለውን ሚና አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል።

በተለይም የንግዱ ማኅበረሰብ ለአገር ውስጥና ለውጭ አገራት የሚያቀርባቸው ምርቶች ጥራትና ደረጃዎችን የጠበቁ እንዲሆኑ ለማስቻል አዲስ ቻምበር የበለጠ መንቀሳቀስ ይኖርበታል ያሉት አቶ ሃሰን፤ በዚህም ለአገር ኢኮኖሚ ማደግ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ማጎልበት ይችላል ሲሉ ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ለአገሪቱ የንግድ ሥርዓት ማደግና መሳለጥ የራሱን አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል፤ ይህንን ጥረቱን በማጎልበት የአገርን ኢኮኖሚ ለማሳደግ የበኩሉን እንደሚወጣ ይጠበቃል ብለዋል።

በሌላ በኩል በ1939 ዓ.ም የተመሰረተውን የአዲስ ቻምበር የ75 ዓመት ጉዞውን የሚያሳይ የፎቶግራፍ ኤግዚቢሽንም ተከፍቷል፡፡

በአፍሪካ የንግድ ምክር ቤቶች ታሪክ ከቀዳሚዎቹ ተርታ የሚሰለፈው የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት/ አዲስ ቻምበር/ የ75ኛ ዓመት ክብረ በዓል ከሰኔ 21 እስከ ሰኔ 23 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ እየተከበረ ይገኛል።

## ርዕሰ አንቀፅ

# ሰላም የአስተዋዮች እና የትውልድ ተሻጋሪ ባለተስፋዎች ዜማ ነው!

መንግስት ከለውጥ ማግስት ጀምሮ በብዙ የህዝብ መስዋእትነት የተገኘውን ለውጥ በሰላማዊ መንገድ መርቶ ለውጤት ለማብቃት ከፍ ያሉ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል። የቀደሙ ቁርሾዎችን በይቅርታና በፍቅር አሸንፎ መሻገር የሚያስችሉ የፖለቲካ ውሳኔዎችን ከማስተላለፍ ጀምሮ በጉዳዩ ላይ ያለውን ቁርጠኝነት በተጨባጭ ማሳየት ችሏል።

አሸባሪው ሕወሓት በስልጣን ዘመኑ የፈጸማቸውን ግፎችና ዘረፋዎች በመተው ቀጣይ የፖለቲካ ምእራፉን በሰላም መቀጠል የሚችልበትን እድል ከመፍጠር ጀምሮ ቀደም ባለው ዘመን በፖለቲካ አስተሳሰባቸው ምክንያት በስደት ላይ የነበሩ የፖለቲካ ቡድኖችንና ግለሰቦችን በሰላም ወደ ሀገር እንዲገቡና ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል እንዲያካሄዱ አድርጓል።

በዚህም የኦሮሞ ነጻነት ግንባርን /ኦነግ/ ፤ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህን /ኢዜማ/ ጨምሮ ብዛት ያላቸው በክልልና በፌዴራል ደረጃ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል በማካሄድ ላይ ናቸው።በዚህም ሀገራዊ የፖለቲካ ምህዳሩ ከመጠፋፋትና ከመሰዳደድ ወጥቶ አቃፊ ሊሆን የሚችልበትን ታሪካዊ እድል መፍጠር ችሏል።

ከዚህም ባለፈ የለውጥ ሀይሉ ህዝባችን በቀደሙት ዘመናት ስለለውጥ የነበረውን አረዳድ በመሰረታዊነት መለወጥ በሚያስችል የሀገርና የህዝብን ጥቅም መሰረት ባደረገ መልኩ ከየትኛውም የፖለቲካ አመለካከት ካለው ቡድን እና ግለሰብ ጋር መኖር የሚያስችለውን የፖለቲካ ቁርጠኛነት ፈጥሮ መንቀሳቀስም ችሏል።

በዚህም ብዙዎች የኢትዮጵያ የፖለቲካ ትንሳኤ መሰረት መጣል ጀምሯል ወደሚል አዲስ ተስፋ ሰጪ የፖለቲካ ትርክት ውስጥ ገብተው ነበር ፤ይህ ጅማሬ ግን የአሸባሪው ሕወሓት እብሪት በወለደው ጀብደኝነት ከፍ ባለ መልኩ ተፈትኗል።በዚህም የለውጡ ጉዞ ከመንገጫገጭ ባለፈ ሀገርና ህዝብ ብዙ ዋጋ የከፈሉበት ታሪካዊ ክስተት ተፈጥሯል።

ከውልደቱ ጀምሮ እራሱን የሴራ ባለሟል አድርጎ የሚወስደውና ከዚህ በሚመነጭ ያልተገባ እብሪት ሁሌም ቢሆን ሰጥቶ ለመቀበል የፖለቲካ መርህ የማይገዛው አሸባሪው ሕወሓት፤ በለውጡ ማግስት የተሰጠውን እድል በመተው ወደ ለመደው የሴራ ፖለቲካ በመጓዝ በተላላኪዎቹ አማካኝነት የሀገርን ሰላም ሲፈታተን ቆይቷል።

በንጹሀን ላይ የአደባባይ ግድያዎችን ከማቀድ እና በተላላኪዎቹ ከማስፈጸም ባለፈ በታዋቂ ሰዎች ላይ ያነጣጠሩ ግድያዎችን በማቀነባበር ሀገርን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ሰላምና መረጋጋትን በማሳጣት ወደ ስልጣን ለመመለስ ብዙ መንገድ ተጉዟል።በዚህም እኩይ ተግባሩም ብዛት ያላቸው ዜጎቻችንን በግፍ ግድያ ለማጣት ተገደናል።

የለውጡን ሀይል ገና በጠዋቱ ለማሰናከል በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ላይ በአደባባይ ግድያን ከማቀነባበር ጀምሮ ፤የለውጥ ሀይሉን ትግስት በመፈታተን ለውጡ ባልተገባ መንገድ እንዲጓዝና እንዲከስም ከፍያሉ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻዎችን ሲያካሄድ ቆይቷል።በዚህም በሀገራዊ የፖለቲካ ምህዳር ላይ መረጋጋት እንዳይታይ አድርጓል።

ይህ ሁሉ የሴራ መንገድ አላዋጣ ሲለው የትግራይን ህዝብ ከሁለት አሰርት በላይ ሲጠብቅ በነበረው የመከላከያ ሰራዊት ላይ "መብረቃዊ ጥቃት "በሚል በተኛበት በማጥቃት ለሰላም ከዛም በላይ ለሀገርና ለህዝብ ያለውን ፍጹም ክህደት እና ንቀት በአደባባይ አሳይቷል። በጥቃቱ ማግስት ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር በማበር ሀገርን እንደ ሀገር የመፍረስ ስጋት ላይ ጥሎ ነበር።

ቀደም ባለው ጊዜም ሆነ ዛሬም ቢሆን ሰላም በማህበረሰብ ህይወት ውስጥ ከፍ ያለ ልእልና እንዳላት ለመስማትም ሆነ ሰምቶ ለመመለስ ፈቃደኝነት ፈጥሮ የማያውቀው ይሕ አሻባሪ ቡድን ፤ከዚህ ሁሉ የሴራ ፖለቲካና ጥፋት በኋላ ዛሬ ላይ ስለ ሰላም ተጨማሪ እድል ተሰጥቶታል። ይህች እድል የመጨረሻ እጣ ፈንታውን የምትወስን ስለመሆኗ የሚጠፋው አይደለም።

እንደቀደመው ዘመን በዚህ እድል ለመቆመር የሚደረግ የትኛውም አይነት ጥረት ፍጻሜው አስከፊ እንደሚሆን፤ ሰላም በብዙ ማስተዋል በሚወለድ ትግዕስት ተስፋ እንደሚደረግ ሁሉ ፤ሊያስከፍል የሚችለውንም የትኛውንም አይነት ዋጋ ከፍሎ ሰላምን ማጽናት እንደሚቻል አሁን ላይ በአግባቡ ማሰብ ተገቢ ነው።

አሸባሪው ሕወሓት ከመቼውም ጊዜ በላይ ሰላም የተሸናፊዎች ሳይሆን የአስተዋዮች እና የትውልድ ተሻጋሪ ባለተስፋዎች ዜማ መሆኑን በአግባቡ ሊረዳው ፤መያዣ ያደረገውን የትግራይ ህዝብ እጣ ፋንታ እንኳን የተሻለ ለማድረግ ዋነኛው አማራጭ ጦር መስበቅ፣ ትውልዶችን በፉከራና ቀረርቶ ልባቸውን ማደንደን እንዳልሆነ ሊረዳ ይገባል።ይህ የጥፋት መንገድ በዚህ ዘመን ማንንም አትራፊ አያደርግም።

የለውጥ ሀይሉ /መንግስት /ለውጡ በሰላም ተጀምሮ እንዲጓዝ የሄደበት መንገድና ለዚህ የከፈለው ዋጋ ብዙ ቢሆንም ፤ለውጡን በመምራት ሂደት ውስጥ ያጋጠሙ ከፍያሉ ተግዳሮቶችን/የሰላም ተግዳሮቶችን/ ከፍ ባለ ትዕግስትና ቁርጠኝነት እየተሻገረ የመጣበት መንገድ የሚበረታታ ነው።ዛሬም ለሰላም እድል ለመስጠት ሁኔታዎችን ማመቻቸቱ የሚደገፍ ነው። ሰላም ትዕግስትንና ማስተዋልን ይፈልጋልና !።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# የስነ ልቡና ጦርነቱን አሸንፎ ለመውጣት

**(አቤል ገ/ኪዳን)**

የምንኖርበት አለም ብዙ ነገሮች የተለመደ ቅርጻቸውን የሚቀይሩበት ወይም የቀየሩበት አለም ነው።ቅርጻቸውን ከቀየሩ ነገሮች መሀከል አንዱ ደግሞ ጦርነት ነው። ዘመናዊው ጦርነት ከጥንቱ በብዙ ነገር ይለያል። በዋነኝነት ከሚለይባቸው ነገሮች መሀከል አንዱ ደግሞ የጦርነቱ አላማ ጠላትን መደምሰስ ሳይሆን የጠላትን የማድረግ አቅም ማሳጣት ላይ ማተኮሩ ነው። ይህ የሆነው በዋነኝነት ለጠላት በማሰብ ሳይሆን ጠላትን ሙሉ ለሙሉ ለማውደም የሚደረገው ጥረት ኢኮኖሚያዊ ጣጣው ብዙ ስለሆነ ነው።

በያዝነው ክፍለ ዘመን በአለም ታሪክ ከየትኛውም ጊዜ በተለየ ጦርነት በከፍተኛ ደረጃ የቀነሰበት ነው። ይህም ጦርነት ከሚፈልገው ከፍ ያለ ኢኮኖሚ አንጻር እንደሆነም ብዙዎች ይስማማሉ፤ ተጨባጭ እውነታውም የሚያመላክተው ይህንኑ ነው። ይህ ማለት ግን የተለመደው ጦርነት ውድ በመሆኑ ቀንሷል ማለት ጦርነት ቀርቷል ማለት አይደለም።

በተቃራኒው ጦርነት ኢኮኖሚያዊ እና ሰብአዊ ኪሳራቸው አነስተኛ በሆኑ ስልቶች እየተቀየረ ከመጣ ውሎ አድሯል። በአነስተኛ ወጪ ጦርነትን በድል ለመወጣት ከተፈበረኩት ስልቶች መሀከል አንዱ እና አሁን በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ እየዋለ ያለው የስነ ልቡና ጦርነት ነው።

የስነ ልቡና ጦርነት ምንድን ነው? በግርድፉ ሲተረጎም እንደሚከተለው ነው "የስነ ልቡና ጦርነት ማለት በጦርነት ወቅት፤ የጦርነት ስጋት ባለበት ወቅት ወይም ቀጠናዊ የጂኦፖለቲካ ውጥረት በሰፈነበት ወቅት ከተግባራዊ ጦርነት ውጭ በታቀደ መልኩ ፕሮፓጋንዳን፤ ማስፈራሪያን እና ሌሎች ቴክኒኮችን በመጠቀም ጠላትን በማደናገር፤ ሞራል እንዲያጣ በማድረግ፤ በማበሳጨት፤ ተስፋ በማስቆረጥ ---ወዘተ ማለት ነው። በአስተሳሰቡ እና በባህሪው ላይ ተጽእኖ መፍጠር ነው"

ይህ ስልት ከዚህ ቀደምም የሚታወቅ ቢሆንም እንኳ በአብዛኛው ጥቅም ላይ የዋለው ግን ከ20ኛው ክፍለ ዘመን መግባት በኋላ ነው። በተለይም ሁለተኛው የአለም ጦርነት ለስነ ልቡና ጦርነት በይፋ ጥቅም ላይ መዋሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። ከዚያ በኋላ ተከትሎ የመጣው ቀዝቃዛው ጦርነት ደግሞ ይህን ሁኔታ ከፍ ባለ ደረጃ እንዲያድግ አድርጎታል። ምእራቡም ምስራቁም አንዳቸው ሌላቸውን በፕሮፓጋንዳ በመውቀር ብዙ ውጤት አግኝተውበታል።

ወደኛ ስንመጣ ይህ ሁኔታ ብዙም የማይታወቅ የነበረ ሲሆን ያለፉት 2 አመታት ግን የስነ ልቡና ጦርነት ምን እንደሚያስከትል በግልጽ የታየበት ነው። በተለይም በአሻባሪው ሕወሓት ላይ የተካሄደው ህግ የማስከበር ዘመቻ እና ያን ተከትሎ የተከሰተው ጦርነት እንዲሁም የምእራባውያኑ አቋም የስነ ልቡና ጦርነቱ በይፋ እንደተከፈተብን አመላካች ሆኗል።

በስነ ልቡና ጦርነቱም ነው አሻሪው ሕወሓት ከተንቤን በረሀ ደብረ ብርሀን የደረሰችው። አሁንም ቢሆን የስነ ልቡናውን ጦርነቱ አፋፍሞ ቀጥሏል።የተጠናከረ የፕሮፓጋንዳ ጦርነት፤ የማያቋርጡ ህዝብን ተስፋ እንዲቆርጥ የሚያደርጉ ወሬዎች፤ ህዝብ ከህዝብ ህዝብ ከመንግስት ህዝብ ከመሪዎቹ እንዲቆራረጥ የሚያደርጉ ተከታታይ የተዛቡ መረጃዎችን በስፋት እየለቀቀ ነው።

በኦነግ ሸኔ እና በብጤዎቹ የሚደረገው ግድያ ከኑሮ ውድነቱ ጋር ተጣምሮ የስነ፣ ልቦናው ጦርነት ዋነኝ አቅም አድርጎ እየተንቀሳቀሰ ነው። በዚህም ህዝብ ሀገሪቱ እየፈረሰች እንደሆነ እና መንግስትም ሆን ብሎ ህዝብን እየጎዳ እንደሆነ እንዲያስብ እየተደረገ ነው። ለዚህ ደግሞ ማህበራዊ ሚዲያው ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ነው።

በመንግስት በኩል ለዚህ ግንባር የሚመክት እሳቤ በቅጡ የተፈጠረ አለመሆኑ ደግሞ የቡድኑን እኩይ ተግባር አቅም እንዲያገን እየረዳው ነው።ሀገራዊ የኮሚኒኬሽን ስራው የተለመደው፤ በተበጣጠሰ እና ትርጉም አልባ በሆነ መልኩ ነው እየተሰራ ያለው።

አሁንም ፌስቡክ ላይ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ንግግር እየቆራረጠ መፖስት ብቸኛ ስራው የሆነ የኮሚኒኬሽን መዋቅር ያለ ይመስላል። ሀገራዊ ሚዲያው በተናበበ እና በተቀናጀ መልኩ የገባንበትን ተግዳሮት በሚመጥን መልኩ መልስ ለመስጠት ዝግጁ አይመስልም።አሁን ላይ ይህን የስነ ልቡና ጦርነት መልሰን መመከት እና መልሰን ማጥቃት ሲገባን በተቃራኒው ችግሩ መኖሩንም እንደ ሀገር የተረዳን አይመስልም።

ልብ ማድረግ የሚገባው የተደራጀ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ የሚካሄደው በዋናነት መንግስት ላይ ይሁን እንጂ ዋነኝ ተልእኮው / ኢላማ ያደረገው ኢትዮጵያ እና ህዝቧ ናቸው።ህዝቡ በብዙ ተስፋ የጀመረውን ለውጥ ማሰናከል ነው።

ስለ ልቡና ግለሰባዊ እና ማህበራዊ ነው።ጥቃቱ የሚያጠነጥነው ግለሰብ ዜጎች ብሎም ማህበረሰብ ላይ ነው።ኢላማው ሰው እና ሀገር ናቸው።ከሀምሌ 1 በኋላ ኑሮ ሰማይ ይነካል፤ ኦነግ ሸኔ አዲስ አበባ በር ላይ ደርሷል፤ መንግስት ለኦነግ ድጋፍ እየሰጠ ስለሆነ ጥቃቱ አይቆምም፤ ንጹሀን እንደ ዶሮ እየታረዱ ነው፤ እነ እገሌ ሀገራት ከኢትዮጵያ መውጣት ለሚፈልግ ፓስፖርት እየሰጡ ነው፤ ወዘተ...የሚሉ ወሬዎች አላማቸው መረጃ መስጠት አይደለም።

አላማቸው ስነ ልቡናን መስለብ ነው።ግባቸው ህዝብን ተስፋ ቆርጦ እንዳይታገላቸው እጅ ማሰጠት ነው።ይህን በሚዲያዎቻቸው ይሰሩታል፤ በሶሻል ሚዲያ ወኪሎቻቸው ያራቡታል፤ የተማረው እና ስልጡኑ የሚባለው፤ መሀል ከተማ ላይ ያለውን በዚህ መልኩ ትጥቅ ካስጣሉ የገጠሩ ህዝብን ደግሞ ስፖንሰር በሚያደርጓቸው እና በሚያስታጥቋቸው ሀይሎች ሰላም ከነሱ ከዚህ በኋላ መንግስትን ለመጣልም ሆነ ሀገሪቱን ለማፍረስ የሚያግዳቸው አንዳች ሀይል አይኖርም።

ለዚሕ ለቡድኑ እኩይ ተልእኮ አሁን መንቃት አለብን። የስነ ልቡና ጦርነት እንደተከፈተብን ማመን እና በዚያ ልክ መደራጀት አስፈላጊ ነው።ለመከላከያው፤ ለፌዴራል ፖሊሱ፤ ለልዩ ሀይሉ፤ ለደህንነቱ፤ ለሳይበር መከላከያ ክንፉ የሚደረገው ድጋፍ ሁሉ የስነ ልቡና ጦርነትን ለሚፋለመው አካል ተደርጎ የመመከት ስራ መስራት ያስፈልጋል።

አልያም መከላከያው ተስፋ የቆረጠ ህዝብን ከኋላው አድርጎ ሊዋጋ እና ሊያሸንፍ አይችልም። ፌዴራል ፖሊሱ ሀገራዊ ስሜቱ በሞተ ህዝብ መሀል ህግን ሊያስከብር አይችልም። ሌላውም እንደዛው።እና ማጠቃለያው መንግስት አሁን የጀመረውን የጸረ ስነ ልቡና ጦርነት ቡድን ግንባታ ማፋጠን አለበት።

# ነፃ ሃሳብ



**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ጽሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# የሀሰተኛ ትርክት መጨረሻ...

## እንደ መውጫ

ዛሬ በመውጫው መግባት ስለአሰኘኝ በመውጫው ገብቻለሁ። አንዳንዴ መውጫችን መግቢያም ሲሆን አቋራጭ ስለሚሆን ድካም ይቀንሳል። ጊዜም ይቆጥባል። በነገራችን ላይ ወደ ገደለው ለሚሉ የአራዳ ልጆችም ስል ጭምር ነው ማጠቃለያዬን ወይም መውጫዬን መግቢያዬ ያደረኩት። መንግስት ዜጎችን ለልዩነት፣ ለመጠራጠር፣ ለግጭት የሚዳርጉ የፈጠራ ትርክቶችን በገለልተኛ የታሪክ ልሒቃንና በሚመለከታቸው ምሁራን አማካኝነት አስጠንቶ የማያዳግም መቋጫ ሊያበጅ የጥል ግድግዳውን ሊያፈርስ ይገባል። እነ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴና ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ደጋግመው ባቀረቡት ምክረ ሀሳብ መሰረት ታሪካችንን መፈተሽ እንደ ገና መበየን ይጠይቃል።ይህን ስል እንደ በጀት ታሪክ በቀመር ይደልደል ማለቴ እንዳልሆነ ልብ ይሏል።

አማራ እንደ ሕዝብም ሆነ እንደ ገዥ መደብ ኦሮሞን ጨቁኗል? አማራ የሚባል ገዥ መደብስ በእርግጥ ነበረ? አማርኛ የተናገረው ገዥ ሁሉስ አማራ ነው? ገዥ መደቡ ኦሮሞውን ከአማራው በተለየ ሁኔታ ጨቁኖት ነበር? በእርግጥ ኦሮሞው ተጨቁኖ ቢሆን ኖሮ እንዲህ እንደ ዋርካ እንደሰፋ ባህሉን፣ ወጉን፣ ታሪኩንና ቋንቋውን አስጠብቆ ይቀጥል ነበር? ተረካችንንና ንጽጽራችንንስ ዘመነ ጓዴነትን/cont mporaries/የተከተለ ነው ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች በገለልተኛ አካል ተጠንተው ምላሽ ቢያገኙ የሀሰተኛ ትርክት ልፋፌ ነቢቡን ምስ ሊያስጥሉት ይችላሉ። አሸባሪው ሕወሓት ወደ አገዛዝ ከመጣ በኋላም በአገዛዝ ላይ ለመቆየት ሲል ኦሮሞንና አማራን መለያየት ስለነበረበት ላለፉት 50 አመታት ጥላቻንና ልዩነት መዋቅራዊ አድርጎ ሰርቶበታል። ሕገ መንግስት ቀርጿል። ህውልት አቁሟል። ይህ አልበቃ ብሎት እንደ ሸኔ ያሉ አሸባሪ ተላላኪዎችን ስፖንሰር በማድረግ ንጹሐንን እያስጨፈጨፈ ይገኛል።

ሌላው በማንነትና በጎሳ ላይ የተዋቀረውን ሕገ መንግስትንም ሆነ ሀገረ መንግስት ስለማለዘብም የተጀመሩ ጥረቶች ሊጠናከሩ፤ በጎሳ ላይ የተመሰረተ ፖለቲካዊ አደረጃጀትም በሒደት መውጫ ሊበጅለትና ፊት ሊነሳ ይገባል። በማንነት ላይ የተመሠረተ ፖለቲካዊ መዋቅሩን ይዞ ብልጽግናን ማረጋገጥ አይቻልም። ከፍ ሲልም ከ50 አመታት በኋላ ሒሳብ ስንተሳሰብ ከአተረፍነው ይልቅ የከሰርነው የትየለሌ ነውና። ከልዩነት ይልቅ አንድነትና ኢትዮጵያዊነት ላይ ተጠናክሮ ሊሰራ፤ ፖለቲካችንም በማንነት ሳይሆን በሀሳብ ሊጎለብት ሊታነፅ ግድ ይላል።

ይሄን የምለው የግለሰብ ነጻነት ከተከበረ የቡድን መብትም ይከበራል በሚል ማፅቀፍ ነው። አንድነት ስል አንድ አይነትነት ማለቴም አይደለም። በከፊል አቅጣጫውን የሳተውና የጥራት እጥረት ያኮሰመነው ስርዓተ ትምህርትም መለስ ብሎ የመፈተሹ ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። ከዚህ ጎን ለጎን ብሔራዊ እርቅና እውነትን የማፈላለግ እና በሕወሓት የሴራ ደማሚት የፈረሱ የሕዝብ ለሕዝብ መገናኛ ድልድዮች መልሰው መጠገን አለባቸው።

ግማሽ ክፍለ ዘመን የተሻገረው ከብጥብጥና እርስ በእርስ በጥርጣሬና በጥላቻ ከመተያየት በቀር ብዙ ያላተረፈልን የብሔር፣ የፈጠራና የሀሰት ትርክት ልፋፌ ነቢብ እስከ ገቢር ያለው ምዕራፍ፣ ቀይ መፅሐፍ እልባት ሊያገኝ ይገባል። የፈጠራ ትርክት ልፋፌ ነቢብ ከተቀዳበት ታሪካችን ብንነሳ ሁላችንም ባለዕዳ ነን። ሁላችንም ባለዕዳ ከሆን ደግሞ የየራሳችንን የፈጠራ ትርክት መቅረጽ እንችላለን። ችሎታችን ግን ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ነው የሚሆነው። ማናችንም አናተርፍም። የዜሮ ድምር ፖለቲካ እንዲሉ። ባለቅኔውና ወግ ሰላቂው በውቀቱ ስዩም ይሄን ወርክብ ከሌላ ማዕዘን ይመለከተዋል።

“ከአሜን ባሻገር” በተሰኘ ከተለመደ ስራው ወጣ ባለ መፅሐፉ፤ “...ኢትዮጵያ ውስጥ ‘ ለታሪካዊ በደሎች እውቅና መስጠት ‘ የሚለው አጀንዳ የተወሰነ የማህበረሰብ ክፍል የዴሞክራሲና የፍትሕ ጥያቄ እንዳያነሳ ማፈኛ ዘዴ ነው። ... ባለፉት ሁለት/ሶስት አስርት አመታት በኦሮሚያ፣ በደቡብና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብዙ ሰላማዊ የአንድ ብሔር ተወላጆች በግፍ የተገደሉትና የተፈናቀሉት የታሪክ እዳ ተሸካሚ ናችሁ በሚል ጦስ ነው” ይላል።

ሰኔ 11 ቀን 2014 ዓም በምዕራብ ወለጋና በጋምቤላ በንጹሐን ላይ የተፈጸመው ጭፍጨፋ፤ በሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም የአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳ ግድያና እሱን ተከትሎ በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ከተሞች በተለይ በሻሸመኔና በባሌ አንድን እምነትና ማንነት ለይቶ የተፈጸመው ግፍ ግን ያለፉት 27 አመታት ቅርሻ ብቻ ሳይሆን መረር፣ ጨከን ያለና ቀድሞ በደንብ የተመከረበትና የተዘከረበት የሚመስል ነው። በእውቀቱ እንዳለው በታሪክ ተሸካሚነቱ ሲከፍለው ከነበረው አበሳ በላይ ሆኖ ነው ያገኘሁት።ምንም እንኳ የታሪክ እዳ እንተሳሰብ ከተባለ ከራስ ስሁል ሚካኤል ተነስቶ በአሉላ አባ ነጋ በኩል አርጎ በአፄ ዮሐንስ አልፎ ከቱሉማና ከጃዊ ጎሳ ወገን ከነበረው የዘመኑ አባዱላ ጉጂ ላይ ይደርሳል ይላል ባለቅኔው። ያው ሁሉም ባለዳ ነው ለማለት ነው። እዚህ ላይ ከአባ ዱላ ጋር በአጋጣሚ ሞክሼ መሆኑን ያዙልኝ። ሬነ የተባለ ሊቅ፣ “ ሀገር ምንድናት “ በተባለ ስመ ጥር ስብከቱ፤ “ ሰዎች ሀገር ለመገንባት ከፈለጉ በታሪክ ውስጥ የተፈጸሙ አንዳንድ ግፎችን ለመርሳት ዝግጁ መሆን አለባቸው። “ ይላል። እስከ ዛሬ ድረስ በሰለባነት ተለይቶ ግፍ እየተፈፀመበት ያለው ማህበረሰብ ከዚህ የሬነ ምክረ ሀሳብ መጸነስና መቀንቀን በፊት ሀገር ለመገንባት ሲል የተፈጸሙበትን ሁሉ ግፎች ቢተውም ዛሬም የግፈኞች ሰለባ እንደሆነ ቀጥሏል።

ሌሎች ማህበረሰቦች ስለ ሀገር፣ ስለ አብሮ መኖር፣ ስለ ይቅርባይነት ሲሉ፣ ወዘተረፈ ሸክሙን፣ ጥቃቱን፣ በደሉንና ግፉን ካላገዙትና ካልተጋሩት ለብቻው እስከ ምን ድረስ ሊቀጥል ይችላል? እገዛና መጋራት ያልሁት እንደሱ ተበደሉ፣ ተጠቁ ለማለት ሳይሆን ከጥላቻ ፖለቲካ እና ከፈጠራ ትርክት ምርኮኝነት መላቀቅ በራሱ ሸክሙን ማገዝ ነው። ይህን ማድረግ ካልተቻለ መጪው ጊዜ ከባድ መሆኑን ለማሚረት ሞራ ገላጭ መሆን አይጠይቅም። በዚህ ማህበረሰብ ላይ እየተፈጸመ ያለውን ዘግናኝ ግፍ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ያለምንም ማቅማማት፣ መሸፋፈንና ማመንታት በአንድ ድምፅ በማውገዝ ሸክሙን የመጋራት ሒደቱን ሀ ብሎ ሊቀላቀል ይችላል። ዛሬም ቢዘገይም አልረፈደም።

እየተፈፀመበት ያለውን ጥቃት በግልጽ ፍርጥርጥ አድርጎ መነጋገርና እውቅና መስጠት፤ ህመሙንና ቁስሉን የመሸከም ሌላ ጅምር ነውና በተለይ ሸኔ ሰኔ 11 ቀን በምዕራብ ወለጋ ጊምቢ ወረዳ በብዙ መቶዎች በሚቆጠሩ ሕጻናት፣ ሴቶች፣ አረጋውያንና ንጹሐን ላይ የተፈጸመው ለመስማት የሚሰቀጥጥ፤ ለማየት የሚዘገንን ጭፍጨፋ ያለ ልዩነት ማውገዝ ያስፈልጋል።

በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ወለጋ ዞን ጊምቢ ወረዳ ቶሌ ቀበሌ እና በጋምቤላ ክልል የተፈጸመው ጭፍጨፋም ሆነ ባለፉት አራት አመታት ማንነትን ኢላማ አድርገው በንጹሐን ላይ የተፈጸሙ ጥቃቶች በዘግናኝነታቸው፣ በአረመኔያዊነታቸው በጭካኔያቸው የከፉ ናቸው። ድርጊቱን መስማት ይረብሻል። ያማል። ስለ ነገዋ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን እጣ ፈንታ እንድንቆዝም አድርጎናል። በተለይ ከሁለት አመታት በፊት የአርቲስት ሀጫሉን ግድያ ተከትሎ ሰኔ 22 ለ23 አጥቢያ ተጀምሮ ለቀናት የቀጠለው ግፍ፤ የተዶለተ በቂ ዝግጅትና ጥናት የተደረገበት ስለመሆኑ ጭፍጨፋውን ይፈፅሙና ይመሩ የነበሩ እኩያን የሰለባዎቻቸውን ማንነትና የመኖሪያ አድራሻ በጹሑፍ በዝርዝር ይዘው እየተመላለሱና እየደጋገሙ እልቂቱን መፈጸማቸው ነው።ይህን ላዳመጠና ለተመለከተ የተፈጸመው ግፍ ስርዓትን ከማቆም፣ ሰላምንና መረጋጋትን ከማስፈን፣ ፍትሕና ርዕትን፣ የሕግ የበላይነትን ከማረጋገጥ በላይ በጥልቀትና ሀቀኝነት ማጣራትን የሚጠይቅ ነው። ሀጫሉ በተገደለ በሰዓታት ልዩነት የተቀነባበረና የተጠና በተቀጣጣይ ፈንጅ የሚታገዝ ሽብር መፈጸምም ሆነ ለመፈጸም ከግብታዊነት የተሻገረ ቅድመ ዝግጅትንና ማቀድን ይጠይቃል። በአንድ ወረዳ በአንድ ጀምበር 38 የሕዝብ ንብረት የሆኑ ተቋማትን በእሳት ማጋየትና ማውደም በደም ፍላት የተፈጸመ ሊሆን አይችልም። የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ አቃቢ ሕግ ፋና ቴሌቪዥን ላይ ቀርበው

“የአርቲስት ሀጫሉ ግድያ ሰበብ ነው፤ “ ያሉትን እዚህ ላይ ልብ ይሏል።

በኦሮሚያ በተለይ በምዕራብ ወለጋ፣ በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በደቡብና በሌሎች ክልሎችና አካባቢዎች የተፈጸሙ ማንነትን ኢላማ ያደረጉ ጭፍጨፋዎችን በዘላቂነት ለማስቆም ከጀርባ ያሉ መግፌኤዎችን በገለልተኛ አካል አጥንቶ መለየት ይጠይቃል። ከጭፍጨፋዎች በፊት ሴራዎች የተሸረቡበትን፤ ደባዎች የተዶለቱበትን አግባቦች መመርመር፤ ነጥቦችን አገናኝቶ ትርጉም ያለው ምስል ላይ መድረስ እና በዘላቂነት ከምንጩ ማድረቅ የግድ ይላል። በዘመነ ቴክኖሎጂ እንደ ሸኔ ያሉ አሸባሪዎችን ዕንቅስቃሴ ተከታትሎና የመገናኛ ዘዴዎቻቸውን ጠልፎ እየፈጸሟቸው ያሉትን ጭፍጨፋዎች አበክሮ ለምን መከላከልና ማስቆም አልተቻለም የሚለውም መልስ የሚሻ ጥያቄ ነው።

ቤት ንብረታቸው ተቃጥሎ ፈሪሃ እግዚአብሔር/አላህ ባደረባቸው ኦሮሞ ጎረቤቶቻቸው ከለላ ከሞት ተርፈው በየቤተ ክርስቲያናቱ ተጠልለው ይገኙ በነበሩ ወገኖች የጭፍጨፋው መሀንዲሶች፤ “ለቃችሁ ካልወጣችሁ ማንም አያስጥላችሁም! አያድናችሁም! አይደርስላችሁም! ቀዬአችንን ከተማችንን ለቃችሁ ውጡ፤ “ የሚል ዛቻና ማስፈራሪያ ያደርሱባቸው እንደነበረ የሚያስታውስ ዜጋ ከጭፍጨፋው ለተረፉ የዛሬዎች ወገኖቹ ምን ዋስትና አላቸው ብሎ ቢጠይቅና ቢሰጋ ሊያስገርም አይገባም።

የሚያሳዝነው ያን ሁሉ ዘግናኝ ግፍና ሰቆቃ በመፈጸሙ ምንም ጸጸት ያልተሰማው አሸባሪ ቡድን የትላንቱን ጭፍጨፋ ከመድገም እንደማይመለስ እንደሰጋሁት ሰሞነኛውን ጨምሮ በርካታ ቅስምና ልብ ሰባሪ ጭፍጨፋዎች በተለይ አንድን ብሔር ኢላማ አድርገው ተፈጽመዋል። እነዚህን የጥፋት ኃይሎች ከጀርባ ሆኖ አይዟችሁ የሚላቸው የጦር መሳሪያና ገንዘብ የሚያቀርብላቸው ማነው? በእርግጥ ከሕወሓት በተጨማሪ ሌላ ኃይልስ ከጀርባ የለም ወይ? ያ ሁሉ ግፍ ሲፈፀም የአካባቢው የአስተዳደርና የጸጥታ መዋቅር ሆነ የክልሉ ልዩ ኃይልስ ለምን የንጹሀንን ህይወት መታደግ አቃተው ? ለእነዚህ ጥያቄዎች የግፉ ሰለባዎች፣ ቤተሰቦችና መላ ሕዝቡ ግልጽ መልስ ይፈልጋሉ።

የክልሉ የአስተዳደርም ሆነ የጸጥታ መዋቅር ከላይ እስከታች ድረስ ለውጡን ከአንገት ሳይሆን ከአንጀት አምኖ ተቀብሎታል ወይ የሚለው ጥያቄ እዚህ ላይ እንደገና ማንሳት ተገቢ ነው። በነገራችን ላይ ይህ ጥያቄ የሚነሳው ለሁሉም የብልፅግና ፓርቲ ነው። በቀዳማይ ትህነግ/ኢህአዴግ ትዝታ ዛሬም የሚተክዙና የሚቆዝሙ አባላት፣ አሰራሮችና አደረጃጀቶች ቁጥር ቀላል አይደለምና። ደጅ ከቆሙ ተፎካካሪዎችና አክቲቪስቶች እንደ ኦነግ፣ ኢዜማ፣ አፌኮ፣ አብን፣ ከኢጋዴን ነጻ አውጭ፣ ከሲአን፣ ወዘተረፈ ካሉት ጋር ልቡ የሸፈተ፤ አንድ እግሩ ብልፅግና ሌላው እግሩ ውጭ የሆነ፣ ቀን ቀን ብልፅግና ብልፅግና እየተጫወተ መሸት ሲል ሸኔ ሸኔ፣ ኢዜማ ኢዜማ፣ አብን አብን፣ ወዘተረፈ የሚጫወተው ቁጥርም ቀላል አይደለም።

የአርቲስት ሀጫሉን ግድያ ተከትሎ የግፉ ማዕከል epicenter በነበረችው ሻሸመኔም ሆነ ባሌ ( አጋርፋ )፣ ባቱ ከተሞች በተፈጸሙ ቀውሶች ቁጥሩ ቀላል የማይባል የብልፅግና አመራርና የጸጥታ መዋቅር አባላት የዜጎችን፣ ሀብት ንብረታቸውንና የህዝብ የልማት ተቋማት መታደግ፣ መከላከልና መጠበቅ ሲገባቸው የጥፋቱ ተባባሪና ተሳታፊ ከመሆናቸው ባሻገር ቀውሱ ሲከሰት የተጣለባቸውን ድርጅታዊም ሆነ ሕዝባዊ ኃላፊነታቸውን፣ ቃል የገቡለትን አደራ መወጣት ሲገባቸው ስልካቸውን አጥፍተው መጥፋታቸው፤ በእርግጥ የብልፅግና መዋቅር መሬት ላይ አለ እስከማለት ደርሰው ነበር። ያም ሆነ ይህ የኦሮሚያ ብልፅግናም ሆነ ሌሎች መዋቅራቸውን በደንብ መፈተሽ ማጥራት ይጠበቅባቸዋል።

ለዚህ ሁሉ ሀገራዊ ቀውስ፣ ሰቆቃና ግፍ አስኳል በሆነው አሸባሪው ሕወሓት ነው። ከዚህ ቡድን ጋር ከአንድም ሁለት ጊዜ ወደ ጦርነት ገብተናል። ሶስተኛ ዙር ጦርነት ላለመቀስቀሱም ዋስትና የለንም። በቅድመ ጦርነቱም ሆነ በድህረ ጦርነቱ እንደ ሀገር የከፈልነው ዋጋም ምን ያህል ግዙፍ እንደሆነ የምንዘነጋው አይደለም።

በየትኛውም አለም በ21ኛው ክፍለ ዘመን በሀገር አንጡራ ሀብት፣ በግብር ከፋዩ ገንዘብ እና በሀገር መሰረተ ልማት ሀገረ መንግስቱን ለማፍረስ፣ ሕገ መንግስቱን ለመናድ፣ የእርስበርስ ግጭት ለመቀስቀስ፣ በሀገሪቱ መሪ ላይ የግድያ ሙከራ አርጎ፣ የሀገሪቱን ሀብት በጠራራ በአደባባይ ዘርፎ፣ ለ30 አመታት በዜጎች ላይ የከፋ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ጥሰት ፈፅሞ፣ ሀሳባቸውን የገለጹ ዜጎችን በጅምላ አስሮ ያሰቃየ፣ የገረፈ፣ አካል ያጎደለ፣ የገደለ፣ ወዘተረፈ፤ እንደ አፄ ልብነድንግል “ጦር አውርድ! “ እያለ ምድርን 40 ጅራፍ እያስገረፈ፣ የጎበዝ አለቃ ሆኖ፣ የሀገርን ብሔራዊ ጥቅምን ለመሸጥ ላይ ታች እያለ፣ ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር እየዶለተ፣ የሕግ የበላይነትን እየጣሰ፣ ሕዝብን አግቶ እና በመንግስት ውስጥ ሌላ መንግስት ሆኖ እያለ፤የለውጥ ኃይሉ ይሄን እፉኝት ቡድን በተለያዩ ተቀባይነት ሊኖራቸውና ላይኖራቸው በማይችሉ ምክንያቶች በጊዜ እርምጃ ባለመውሰዱ አፈር ልሶ ሊነሳ ችሏል።

ከግብፅ፣ ከሸኔና ከሌሎች የጥፋት ኃይሎች ጋር ግንባር በመፍጠር ለውጡን ለማኮላሸት፣ የርስ በርስ ግጭት ለመለኮስ፣ ሀገር ለማፈራረስና በሕዝባዊ ትግል የተነጠቀውን ስልጣን በአቋራጭ ለመያዝ ሌት ተቀን እየማሰነ ይገኛል። የአርቲስት ሀጫሉ ግድያና እሱን ተከትሎ የተከተለው ሁከትም ሰሞኑን በጊምቢ ወረዳና በጋምቤላ ከተማ የተፈጸመው ጭፍጨፋ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው።

**ሀገራችን ኢትዮጵያንና ሕዝቧን እንደ ሰሞኑ ካለ ጭፍጨፋና ሰቆቃ ፈጣሪ አብዝቶ ይጠብቃት!**

**አሜን።**

# የነገን ተስፋ ያሳየን ጉብኝት

**አቤል ገ/ኪዳን**

ባለፈው ሰሞን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እኔን እና ሌሎች ጥቂት ሰዎችን የጸጥታ ተቋማትን እንድንጎበኝ ጋብዞን ነበር። ተጋባዦቹ ከሁሉም የሙያ ዘርፎች የተጋበዝን ነን ማለት እንችላለን። ከኪነ ጥበብ ሰዎች ፋንቱ ማንዶዬ እና ደበሽ ተመስገን ፤ ከፖለቲከኞች አንዱአለም ቤኬቶ ፤ ከአክቲቪስቶች ስዩም ተሾመ፤ ከጋዜጠኞች ጌጡ ተመስገን ፤ ከምሁራን ኢንጂነር ጌታሁን ሄራሞ እና ዶ/ር ወዳጄነህ መሀረነ ፤ ከቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ሰለሞን ካሳ (ቴክቶክ ዊዝ ሰለሞን) ወዘተ.. መጥቀስ እንችላለን። በጥቅሉ ባለሙያዎች በየአይነቱ የተሰባሰቡበት ጉብኝት ነበር።

ጉብኝቱ የተጀመረው ከኢፌዴሪ አየር ሃይል ነበር። ቦታውም ቢሾፍቱ ነው። ማልደን ስንደርስ የተቀበሉን ዋና አዛዡ ጄነራል ይልማ መርዳሳ እና ምክትሎቻቸው ናቸው። ጊቢው መቼም ተውቧል የሚለው ቃል አይገልጸውም። ከአጥሩ ጀምሮ ሁሉም ነገር በውብ ሁኔታ የተሰራ ነው። የበለጠው አግራሞት ግን ገና ከፊታችን እየጠበቀን ነበር። አየር ሃይሉ ጊቢ ከማስዋብም ባለፈ ብዙ ስራ ሰርቷል። ከዚህ ቀደም አየር ሃይልን የሚያውቅ ሰው የቢሾፍቱው ጊቢ ሰፊ ባድማ ነበር።

አሁን ግን ጊቢው ሙሉ አረንጓዴ ነው። ምቹ የአስፋልት መንገድ ተሰርቶለታል። ህንጻዎቹ በፍጹም ጥራት ታድሰዋል። ቴክኖሎጂ ጊቢው ውስጥ ዘልቋል። ሁለት ነገሮች ግን የበለጠ አድናቆት የሚገባቸው ናቸው። አንደኛው ነገር አየር ሃይሉ ጊቢውን ከማስዋብ ባለፈ በወታደራዊውም ዘርፍ ብዙ ስራዎችን እየሰራ መሆኑ ነው። የኢንጂነሪንግ ክፍሉ በተለይ አስደናቂ ስራዎችን እየሰራ ነው። በትምህርት ዘርፍም ብዙ እየተሰራ ነው።

አንድ አየር ሃይል ሊኖረው የሚገባውን ቁመና እየያዘ ነው። ሁለተኛው አስደናቂ ነገር ደግሞ የአየር ሃይሉ መሪዎች ከፖለቲከኛ ይልቅ ወታደራዊ ለዛ የሚኀላባቸው መሆናቸው ነው። በሁሉም ላይ ጥሩ መንፈስ እና የራስ መተማመን ይታያል። ምድሩም ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሰማይም የኛ ነው ሲሉ በኩራት ነው። ከዚህ ቀደም አየር ሃይሉ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ ሠራዊቱ ከሕዝባዊነት ይልቅ ፓርቲያዊ ለዛ ነበር። አሁን ያ ጠረን ጠፍቷል።

ከአየር ሃይል ቀጥሎ የተጓዝነው አዲስ አበባ ወደሚገኘው የመከላከያ ዋና ጽ/ቤት ነበር። እዚህ ደግሞ ሌላ አስደናቂ ነገር አየን። ከ13 ዓአመታት መጓተት በኋላ በጣም ግዙፍ ህንጻ ተገንብቷል። ህንጻው ግዙፍ ብቻ ሳይሆን በጣም ዘመናዊ ነው። በመቶዎች የሚቆጠሩ ቢሮዎች ፤ ብዙ ማእድ ቤቶች ፤ እንግዳ መቀበያዎች ፤ የስብሰባ አዳራሾች አሉት። ሁሉም ጽዱ ናቸው። በዚያኑ ልክ ግን በጣም ዘመናዊ ናቸው።



የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ህንፃ

**የተቋሙ ቅጽር ጊቢ ውስጥ ተሳስታ የምትገባ ወፍ እንኳን የሚለይ የደህንነት ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡የበለጠ አስደናቂው ነገር ግን ዘመቻ የሚመራበት ቴክኖሎጂ ነው፡፡ፍጹም ዘመናዊ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ጦሩ በአሸባሪው ሕወሓት ወረራ ከገጠመው አደጋ አሁን ሙሉ ለሙሉ አገግሟል፡፡በሰው ሀይልም በትጥቅም ተደራጅቷል፡፡የቴክኖሎጂ ድጋፍ አግኝቷል፡፡ልክ እንደ አየር ሃይሉ ሁሉ የምድር ጦሩም ከፖለቲካ እንደተነጠለ መሪዎቹ በሙሉ እምነት ይናገራሉ፡፡**




የተቋሙ ቅጽር ጊቢ ውስጥ ተሳስታ የምትገባ ወፍ እንኳን የሚለይ የደህንነት ሥርዓት ተዘርግቷል። የበለጠ አስደናቂው ነገር ግን ዘመቻ የሚመራበት ቴክኖሎጂ ነው። ፍጹም ዘመናዊ ሥርዓት ተዘርግቷል። ጦሩ በአሸባሪው ሕወሓት ወረራ ከገጠመው አደጋ አሁን ሙሉ ለሙሉ አገግሟል። በሰው ሃይልም በትጥቅም ተደራጅቷል። የቴክኖሎጂ ድጋፍ አግኝቷል። ልክ እንደ አየር ሃይሉ ሁሉ የምድር ጦሩም ከፖለቲካ እንደተነጠለ መሪዎቹ በሙሉ እምነት ይናገራሉ።

የሁለተኛው ቀን ጉብኝታችን የተጀመረው ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ነው። ቦሌ የሚገኘው ህንጻ ፍጹም ውብ ነው። በቅርቡ ነው የተመረቀው። ህንጻው ውብ ቢሆንም ከባድ ውጊያ የሚካሄድበት ቦታ ነው። ውጊያው የሳይበር ነው። በባንኮቻችን ፤ በግድቦቻችን ፤ በጸጥታ ተቋማቶቻችን እና ሌሎች ላይ በየሰከንዱ የሚደረገውን ጥቃት የሚመክተው እና መልሶ የሚያጠቃው የብሩህ አእምሮ ኢትዮጵያውያን ስብስብ ያለው እዚህ ነው። ውጊያው 24 ሰአት ነው። ኢንሳም 24 ሰአት ይሰራል።

ከሁሉ በላይ አስደሳቹ ነገር ኢንሳ ውስጥ ያሉ

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

ኢትዮጵያውያን ዓለም አቀፍ ቴክኖሎጂዎችን እንዴት አድርገው ኢትዮጵያዊ እንደሚያደርጉት ማየቱ ነው። ብዙ ድንቅ ጭንቅላት ያላቸው ልጆች ብዙ የፈጠራ ስራዎችን አሳዩን። ድህነት ባይዘን ኖሮ እና እነዚህ ወጣቶች ላይ ተጨማሪ በጀት መመደብ ቢቻል ብዙ ታሪክ እንደሚሰሩ እርግጠኛ ሆንን።

የኢንሳ ቆይታን ስንጨርስ እዚያው ጊቢ ውስጥ የሚገኘውን አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲቲዩት ጎበኘን። ይህ ደግሞ ፈረንጆቹ ጨዋታ ቀያሪ (game changer) የሚባሉ የቴክኖሎጂ ስራዎች እየተሰሩበት ያለ ተቋም ነው። የኢንስቲትዩቱ ወጣት ምሁራን በተለይ ቴክኖሎጂ ለጤና አገልግሎታችን መሻሻል የሚፈጥረው እድል እጅግ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ አሳይተውናል።

ዶክተር ብርቅ በሆነባት ሀገር የሚያስፈልገንን ዶክተር ማፍራት እስክንችል ድረስ ያለን አማራጭ እንዲህ አይነት ቴክኖሎጂን ማላማድ ነውና ተቋሙ እየሰራ ያለው ስራ በጣም የሚደነቅ ነው። ከጤናው ዘርፍ ባለፈ በቋንቋ፤ በሳይበር ደህነንት እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ እየተሰራ ያለው አስደሳች ነው።

ቀጣዩ የጎበኘነው ተቋም ለወትሮው እንኳን ለጉብኝት በበሩ ሲያልፉ እንኳ አተኩሮ ለማየት የሚያስፈራውን የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት ቢሮ ነው። አሁን ግን ተጋብዘን ገባንበት ፤ ይባስ ብሎም ምሳ ተጋበዝንበት። ዋና ዳይሬክተሩ ተመስገን ጥሩነት እና ምክትሎቻቸው በር ድረስ መጥተው ነበር የተቀበሉን። ከዚያም ለወትሮው ድብቅ የነበረው ያ አስፈሪ ተቋም አሁን በብርሃን ምን እንደሚመስል አስረዱን።

እዚህም ቴክኖሎጂ ዋና ተዋናይ ሆኗል። የዚህን ጉብኝት ልዩ የሚያደርገው ደግሞ ብዙ አፈታሪኮች እውነት እንዳልሆኑ ማየታችን ነው። ለምሳሌ ያህል ደህንነት መስሪያ ቤቱ እንዲሁ በማሕበራዊ ሚዲያ መንግሥትን የሚቃወሙ ሰዎችን ስልክ ሲጠልፍ እና ፌስቡክ ሲበረብር የሚውል ይመስለን ነበር።

እዚያ ግን ያየነው መስሪያ ቤቱ ከዚያ የበለጠ ብዙ በሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጭ ያሉ የቤት ስራዎች እንዳሉት ነው። ከዚያም ባለፈ ተቋሙ ብዙ ስራው በአደባባይ የሚታይ ባይሆንም እንኳ እንደማንኛውም መስሪያ ቤት እንደሆነ እና አሁን ከለውጡ ወዲህ ደግሞ ሀገሪቱ ላለባት ተግዳሮት በሚመጥን መልኩ አዲስ ጎዳና ላይ እንዳለ ተረድተናል።

ቀጠልን ፤ ጉዞ ወደ ፌዴራል ፖሊስ ዋና ጽ/ቤት። የተቀበሉን ኮሚሽነር ጄነራል ደመላሽ ጥሩነህ ናቸው። እሳቸውም ተቋማቸው እያካሄደ ስላለው ሪፎርም እና ስላገኘው ለውጥ ሲያወሩ በኩራት እና በስሜት ነው። አሁን ላይ ተቋሙ የመንግሥትን ትኩረት እንዳገኘ ይናገራሉ። ፌደራል ፖሊስ ላይም አስደናቂው ነገር ተቋሙ ከማኑዋል ወደ ዲጂታል እያደረገ ያለው ሽግግር ነው።

በተለይ የሬዲዮ መቆጣጠሪያ ክፍል ውስጥ ለጎብኚዎች ተቋሙ እያካሄደ ስላለው ለውጥ ያስረዳው ወጣት አባል ላይ ያለው ከፍተኛ ስሜት እና ቅልጥፍና ተቋሙ አሁን ላለበት ወቅታዊ መነቃቃት ጥሩ ማሳያ ነው። ከዚህም ባለፈ በቴክኖሎጂም በሎጀስቲክስም እያሳዩት ያለው እመርታ ይበል የሚያሰኝ ነው።

የነዚህ የጸጥታ ተቋማት ጉብኝታችን አንድ ተስፋ የሰጠን ነገር ቢሆን የተቋም ግንባታ ስራ እየተካሄደ እንደሆነ ነው። ዛሬ ላይ ጠላቶቻችን በሚሸርቡት ሴራ ብዙ ዋጋ እየከፈልን ቢሆንም ይህ የተቋም ግንባታ ሳይቋረጥ ከቀጠለ ግን ነገ ላይ ጠላቶቻችን ሴራ እንዳይሸርቡ ሳይሆን ሴራ እንዳያስቡ አድርገን ማስቆም እንደምንችል እርግጥ ነው።

በሶስተኛው ቀን ጉብኝታችን በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈትቤት ዙሪያ እየተሰሩ ያሉ ስራዎችን ለመጎብኘት እድል አግኝተናል። እርግጥ እነዚህ ግንባታዎች በዚያ በኩል ላለፈ ሰው በግልጽ የሚታዩ ቢሆኑም እንኳ ፕሮጀክቱን የሚመሩት ሰዎች እያስረዱ ሲሆን ደግሞ ነገሩ የበለጠ ትርጉም የሚሰጥ ሆኖ ይገኛል።

ለምሳሌ ያህል አራቱ ቤተ መጻህፍትን ብንመለከት ፋይዳቸው እና ትርጉማቸው በጣም ከፍ ያለ ሆኖ አግኝተነዋል። የአብርሆት ቤተ መጻህፍት ፤ የሳይንስ ሙዚየም ፤ የእጽዋት ማእከል እና የማእድን ጋለሪ እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ችለው መቆም የሚችሉ ጽንሰ ሃሳቦች እና ተቋማት ናቸው። እነዚህ ተቋማት ስለ ነገይቱ



**የአብርሆት ቤተ መጻህፍት ከፊል ገጽታ**

ኢትዮጵያ የሚጠቁሙ የተስፋ ምንጮች ናቸው።

እነዚህ ተቋማት አሁን መገንባታቸው አግባብ እንዳልሆነ የሚያምን ሰው አለ። ከእኛም መሀከል አንዳንዶቻችን ከጉብኙቱ በፊት ያን ስሜት እንጋራ እንደነበር የማይካድ ሀቅ ነው። ነገር ግን በተቋማቱ ውስጥ በአካል ስትገኝ ይህ ስሜትህ አግባብ መሆን አለመሆኑን ትጠራጠራለህ። ተቋማቱ በጣም ውብ እና ግዙፍ ሆነው ነው የተሰሩት። ከውበታቸው እና ከግዝፈታቸው በላይ ግን እንዲይዙ የተፈለገው አላማ በጣም ግዙፍ ነው።

እስከ ዛሬ ኢትዮጵያ ለመድሃኒት እና ለሌላም ተግባር የሚውሉ ብዙ እጽዋት አሏት ስንል ከርመናል። ነገር ግን እነዚያን በስም እንጂ በተግባር የማናውቃቸውን እጽዋት የምናገኘው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጊቢ ባለው የእጽዋት ሙዚየም ነው። ኢትዮጵያ ማእድን አሏት እንላለን ነገር ግን እስከዛሬ የትኛው ማእድን የቱጋ እንዳለ ቢጠየቅ አይደለም ተራው ዜጋ ሚኒስቴሩን የሚመራው ሰው እንኳን አይመልሰውም።

አሁን ግን እያንዳንዱ ማእድን ምን አይነት እንደሆነ እና የትኛው የኢትዮጵያ ክልል ላይ እንደሚገኝ ፤ በምን ያህል መጠንም እንደሚገኝ ማወቅ የሚያስችል ሙዚየም እና ሥርዓት ተሰርቷል። ከሁሉ የሚያምረው እና አስደናቂው ደግሞ የሳይንስ ሙዚየሙ ነው። ግዝፈቱ አንድ ደንበኛ ስቴድየም ነው የሚያክለው። ግንባታው ወደ መጠናቀቁ ነው።

ዓላማው የኢትዮጵያ ልጆች አብርሆት ቤተ መጻህፍት ያነበቡትን ንድፈ ሃሳብ በተግባር እንዲያሳዩበት ነው። ተስፋው ከአሁኑ ምራቅ ያስውጣል። ማንም ጤነኛ የሆነ ሰው እነዚህን 4 ተቋማት ከጎበኘ በኋላ የሚለው አንድ ነገር ቢሆን ለምን ተሰራ ሳይሆን ለምን በሁሉም ክልሎች አይሰራም የሚል ነው።

የብሄራዊ ቤተ መንግሥት የመኪና ፓርኪንግ ፤ ከፓርኪንጉ ወደ አንድነት ፓርክ የሚያስገባው ዋሻ ፤ የወዳጅነት አደባባይ እና በአቅራቢያው ያሉ ሌሎች ፓርኮች ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ህንጻ ፤ የማዘጋጃ ቤት እድሳት ወዘተ… ዘላቂ ሀብቶች ናቸው። ስለ እያንዳንዳቸው ብዙ ማለት ይቻላል።

ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ ውስጥ ተቋማት ግንባታ ያለ ዓላማ የሚካሄድ ነበር። ጉምቱ የሚባሉት ባለሥልጣናት ሥልጣን ሲለቁ ስራ ፈትተው ነገር ከሚተበትቡ ተብለው የተቋቋሙ ተቋማት ፤ የተፈጠሩ አደረጃጀቶች ብዙ ናቸው። ብዙዎቹ በጊዜ ሂደት ከስመዋል። ብዙዎቹ የመመስረት ዓላማቸው ፖለቲካዊ ስለነበር ፖለቲካው

**አራቱ ቤተ መጻህፍትን ብንመለከት ፋይዳቸው እና ትርጉማቸው በጣም ከፍ ያለ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የአብርሆት ቤተ መጻህፍት ፤ የሳይንስ ሙዚየም ፤ የእጽዋት ማእከል እና የማእድን ጋለሪ እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ችለው መቆም የሚችሉ ጽንሰ ሀሳቦች እና ተቋማት ናቸው፡፡**

ሲዛባ አብረው ተናግተዋል። እነዚህ ግን ከፖለቲካ የራቁ ናቸው። ማንም በሥልጣን ላይ ይኑር የሳይንስ ፤ የማእድን፤ የእጽዋት ማእከል ያስፈልገዋል።

የትኛውም መንግሥት የንግድ ባንክን አይነት ግዙፍ ተቋም ቢያገኝ አይጠላም። ሁሉም መሪ ጠንካራ አየር ሃይል ፤ ግዙፍ ምድር ጦር ፤ ከዓለም የሚፎካከር የሳይበር ተዋጊ ፤ እንኳን የተደረገውን ቀርቶ የታሰበውን የሚያውቅ የደህንነት መዋቅር ተሰርቶ ቢጠብቀው ደስተኛ ነው። አሁን እየተሰራ ያለውም ያ ነው። ሁሉም ሰው በብዙ ምክንያት መንግሥት ሊወቅስ ይችላል። እኛ በጎበኘናቸው ተቋማት ግን መንግሥትን ሊያመሰግን ብቻ ነው የሚችለው።

በጉብኝታችን ወቅት በሙሉ ካገኘናቸው ሹማምንት ጋር ጥያቄ የመጠየቅ እድል ስናገኝ ጠይቀናል። ዋነኛ የነበረው ጥያቄ መከላከያው ፤ ፌዴራል ፖሊሱ ፤ ደህንነቱ ፤ ኢንሳው በዚህ ልክ ከተጠናከረ ለምንድን ነው በየቦታው ያለውን የሰው ግድያ ማስቆም ያቃተን የሚል ነበር። ለዚህ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መጨረሻ ላይ የሰጡን ሰፋ ያለ ማብራሪያ ግልጽ ያደረገልን አንድ ሀቅ ቢኖር ግድያውን ለማስቆም ብቸኛው መፍትሄ የተጀመረውን የጸጥታ ተቋማት ግንባታ ማፋጠን እና ማጠናከር ብቸኛው መንገድ እንደሆነ ነው።

የቀይ ባህር እና የአባይ ፖለቲካ ቁጭ ብሎ በማልቀስ፤ መንግሥት በመውቀስ ፤ መሪ በመቀያየር የሚፈታ አይደለም። ብቸኛው መፍትሄ ከፖለቲካ የጸዱ፤ በእውቀት የሚመሩ ፤ በቴክኖሎጂ የዘመኑ ጠንካራ ተቋማትን በመገንባት አቅምን ማሳየት ነው።

የአየር ሃይሉ ጄነራል ይልማ መርዳሳ እንዳሉን ከሆነ፤ አየር ሃይሉን እየገነቡ ያሉት ለመንደር ግርግር ሳይሆን ኢትዮጵያን ከጎረቤቶቿ ጋር ለማከባበር ለጠላቶቿም ምንም ነገር ከማድረጋቸው በፊት ሁለቴ እንዲያስቡ ለማድረግ ነው።

ደህንነቱ እየተሰራ ያለው ለካፌ ወሬ ለቀማ ሳይሆን ከድንበር ወዲያ የሚሸረብብንን ሴራ አንፍንፎ ለማክሸፍ ነው ፤ ኢንሳ እየተገነባ ያለው የግለሰብ ፌስቡክ ለመበርበር ሳይሆን ለታላቁ ዓለምአቀፍ ጦርነት ነው።

አብርሆት እና የሳይንስ ሙዚየም የሚሰሩት ለማትሪክ ፈተና ሳይሆን ለዓለም አቀፉ ፉክክር ብቁ ሃይል ለማዘጋጀት ነው። እየተሰራ ያለው ለነገ ነው። ይህን እንደ ሕዝብ እኛ ባንረዳ ጠላቶቻችን ግን ከአሁኑ ታውቋቸዋል። ለዚህ ነው አሁን ላይ ወጥረው የያዙን። ጉብኝትቱም ከዛሬው ክስተት በላይ የነገ ተስፋችንን ያየንበት ነውና አስደሳች ነበር ማለት ይቻላል።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# ለአርሶ አደሩ ተጠቃሚነት ተስፋ የተጣለበት የኢንዱስትሪ ፓርክ

አንተነህ ቸሬ

*መንግሥት መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን እውን ለማድረግ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል ብሎ ትኩረት ከሰጣቸው ተግባራት መካከል የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት አንዱ ነው። ፓርኮቹ በሚገነቡባቸው አካባቢዎች ለሚኖረው የሕብረተሰብ ክፍል ሥራ በመፍጠርና ከአካባቢው ጋር ተስማሚ የሆነ የሥራ ከባቢ እውን በማድረግ ለሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል።*

የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ተመራጭ ከሚያደርጓቸው ነገሮች መካከል በርካታ አገልግሎቶችን አንድ ሥፍራ ላይ ሰብስብ አድርገው የሚያቀርቡ መሆናቸው፣ ተገቢ መሰረተ ልማት የሚገነባላቸው እንዲሁም ከሌሎች አምራቾች ጋርም የሚያገናኙ መሆናቸው ይጠቀሳሉ። ከዚህ አንፃር በኢትዮጵያም ብዙ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማቋቋም እንዲሁም በቂ የሆነ የሰውና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን፣ ማሽኖችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባትን፣ የብድር አቅርቦትን፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን እና የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን እንደማበረታቻ በማቅረብ ትልልቅ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ፋብሪካዎቻቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲከፍቱ ጥረቶች ተደርገዋል።

በእርግጥም ኢትዮጵያ የአፍሪካ የማምረቻ መናኸሪያ እንድትሆን የሚደረገውን ጥረት ለማቀላጠፍ እንዲሁም የሥራ አጥነት ችግርን ለመቅረፍ ላቅ ያለ ሚና ይጫወታል ተብሎ የተጣለበት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ውጤቶች ተገኝተውበታል። በተለይም ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድሎችን በመፍጠር ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ አበርክተዋል።


የግብርና ውጤቶችን እሴት በመጨመር በብዛትና በጥራት ተወዳዳሪ የማድረግ አቅም እንዳላቸው የታመነባቸው የተቀናጀ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን ያሳካሉ ከተባሉ የኢንዱስትሪ ፓርክ ዘርፎች መካከል በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። እነዚህ የአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለአርሶ አደሮች የግብይት ሰንሰለቱን ቀላል በማድረግ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የገበያ ትስስር ይፈጥራሉ። ባለሀብቶች የግብርና ግብዓቶችን ከአርሶ አደሮች እንዲቀበሉ በማድረግ አርሶ አደሮች የልፋታቸውን ያህል እንዲጠቀሙ አወንታዊ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ።

በኦሮሚያ ክልል፣ ምስራቅ ሸዋ ዞን፣ አዳሚ ቱሉ ወረዳ የሚገኘው የ‹‹ቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ›› በሀገሪቱ ከተገነቡ የተቀናጀ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች (Integrated Agro-Industry Parks) መካከል አንዱ ነው። ፓርኩ በሚያዝያ ወር 2013 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የተመረቀ ሲሆን የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የወተት፣ የማር፣ የስጋና የእንቁላል ምርቶችን የሚያቀነባብሩ አምራቾች የሚሰማሩበት የኢንዱስትሪ ፓርክ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ በፓርኩ ምርቃት ወቅት ‹‹ግብርናችንን በአግሮ ኢንዱስትሪዎች ልማት የበለጠ እናዘምነዋለን። ዛሬ የተመረቀው የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ለግብርናው ዘርፍ፣ ለአርሶ አደሮቻችን እና ለሸማቾች የኢትዮጵያን የብልጽግና ራዕይን የሚያሳይ ነው›› ብለው ነበር።

የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ በ271 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ፓርክ ሲሆን አጠቃላይ ግንባታው 86 በመቶ ደርሷል። እስካሁን ለግንባታው ሰባት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ወጪ የተደረገ ሲሆን ግንባታው ሲጠናቀቅ አጠቃላይ የግንባታው በጀት ከዘጠኝ ቢሊዮን ብር በላይ እንደሚሆንና በ2015 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ ይጠበቃል።

ምንም እንኳ የፓርኩ አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም 86 በመቶ ቢሆንም ባለሀብቶችን ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚችልበት አቅም ላይ ደርሷል። ፓርኩ ባለሀብቶችን ተቀብሎ ለማስተናገድ ባከናወናቸው ተግባራት አንዳንድ አምራች ኩባንያዎችም ወደ ፓርኩ ገብተው በግብርና ምርቶች ማቀነባበር ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችሏቸውን የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እያከናወኑ ይገኛሉ። ማር በማቀነባበር ሥራ ላይ የተሰማራ አንድ አምራች ድርጅት ደግሞ የሙከራ ምርት መጀመሩ ተገልጿል።



ባለሀብቶችን ለመቀበል በዝግጅት ላይ ያለው የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ

በኦሮሚያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የኦፕሬሽን ዘርፍ ኃላፊና የኮርፖሬሽኑ ዋና ስራ አስኪያጅ አማካሪ አቶ መሐመድ ሐሰን አምራቾች ወደ ፓርኩ ገብተው ሥራ እንዲጀምሩ ለማስቻል ሲከናወኑ የቆዩ ተግባራት እንዳሉ ይናገራሉ። እንደእርሳቸው ገለፃ፣ የፓርኩ አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም 86 በመቶ ቢሆንም አሁናዊ የግንባታ ደረጃውና የመሰረተ ልማት አቅርቦት አቅሙ ባለሀብቶች ወደ ፓርኩ ገብተው ሥራ እንዲጀምሩ የሚያስችለው ነው። በመሆኑም ባለሀብቶችን ሥራ ለማስጀመር የሚያስችሉ የመንገድ፣ የውሃ፣ የመብራት፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት፣ የቆሻሻ ማጣሪያና ሌሎች ተያያዥ ግንባታዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል። የቆሻሻ ውሃ ማጣሪያው ከ56 በመቶ በላይ ተጠናቋል።

የኃይል አቅርቦትን በተመለከተ ‹‹የኃይል አቅርቦት ሥራ የሚከናወነው በፌዴራል መንግሥት ነው። በዚህም መሰረት የማከፋፈያ ጣቢያ ግንባታ ተጀምሯል። እስከዚው ድረስ ባለሀብቶች ወደ ፓርኩ መጥተው በመብራት እጥረት እንዳይቸገሩ በማሰብ በኮርፖሬሽኑ ገንዘብ 10 ሜጋ ዋት ኃይል እንዲቀርብ አድርገናል›› ብለዋል። ስለሆነም በአሁኑ ወቅት ባለሀብቶች ወደ ፓርኩ መጥተው ሥራ ለመጀመር የሚያስቸግራቸው ነገር እንደሌለና ከመጡ መስተናገድ እንደሚችሉም አቶ መሐመድ ተናግረዋል።

በኦሮሚያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ባለሥልጣን የጥራት መሰረተ ልማት ዳይሬክተርና የጥራትና የምግብ ደህንነት ግብረኃይል ቡድን መሪ አቶ ጌታቸው ፈይሳ በበኩላቸው፣ የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ባለሀብቶች ወደ ፓርኩ ገብተው ሥራ እንዲጀምሩ የሚያስችሉ ዋና ዋና የመሰረተ ልማት ሥራዎች መከናወናቸውን ይገልፃሉ። የመብራት፣ የመኖሪያ ቤት፣ የውሃ መስመር፣ የህክምና፣ የፖሊስ ጣቢያ፣ የሥልጠናና የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ተዘጋጅተዋል። ፓርኩ በማር፣ በስጋ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በዘይትና በጥራጥሬ ማቀነባበር የሚሰማሩ ባለሀብቶች ይገቡበታል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ከሚቋቋሙባቸው ዓላማዎች መካከል አንዱ ብዙ የሥራ እድሎችን በመፍጠር ዜጎችን የሥራ ባለቤትና አምራች ማድረግ እንደሆነ ይታወቃል። በዚህ ረገድ የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ በግንባታው ሂደት ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል ፈጥሯል። በቀጣይም በተለያዩ የፓርኩ የሥራ ደረጃዎች ብዙ የሥራ እድሎች እንደሚፈጠሩ ይጠበቃል።

አቶ መሐመድ የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ስለፈጠራቸውና ወደፊትም ስለሚያስገኛቸው የሥራ እድሎችና ሌሎች ጥቅሞች ሲያስረዱ ‹‹ፓርኩ በተገነባበት አካባቢ የሚገኘው የሕብረተሰብ ክፍል በተለያዩ መንገዶችና ደረጃዎች ተጠቃሚ ይሆናል። በፓርኩ ግንባታ ወቅት በተፈጠሩ የሥራ እድሎች በርካታ ሰዎች ተጠቃሚ ሆነዋል። ለፓርኩ ግብዓት የሚያቀርቡ ስድስት የገጠር ሽግግር ማዕከላት ተቋቁመዋል፤ በግንባታው ወቅት ጥሬ እቃዎችንና የግንባታ ግብዓቶችን የሚያቀርቡ ማሕበራት እንዲሁም አገልግሎት የሚሰጡ (የምግብ ዝግጅት፣ የመስተንግዶ ...) አካላትም አሉ። እነዚህ የሕብረተሰብ ክፍሎች በሥራ እድል ተጠቃሚ ሆነዋል። በሌላ በኩል በልማት ተነሺ ከሆኑ የአካባቢው የሕብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ወጣቶችንም ከባለሀብቶች ጋር በማገናኘት የሥራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል። በአጠቃላይ በፓርኩ የግንባታ ሂደት ለ13 ሺ የአካባቢው ነዋሪዎች የሥራ እድል መፍጠር ተችሏል።

ባለሀብቶች ወደ ፓርኩ ገብተው ሼዶችን በመገንባት ሂደት የሚፈጠሩ የሥራ እድሎችም አሉ። ወደ ፓርኩ የገቡ ባለሀብቶች ግንባታቸውን ጨርሰው ወደማምረት ሲሸጋገሩ ተጨማሪ የሥራ እድሎች ይፈጠራሉ። አርሶ አደሩ ለባለሀብቶች ግብዓት ሲያቀርብ በግብርና ቦታ ላይ በሚከናወኑ ሥራዎች (መዝራት፣ መንከባከብ፣ ምርት መሰብሰብ ...) ለአካባቢው ሕብረተሰብ የሚፈጠሩ የሥራ እድሎችም ፓርኩ ያስገኛቸውና ወደፊትም የሚያስገኛቸው ጥቅሞች ናቸው›› በማለት ያስረዳሉ።

የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ የግብርና ውጤቶችን በማቀነባበር ላይ አተኩሮ የሚሰራ እንደሆነ ይታወቃል። በዚህ ሂደት ለፓርኩ ምርቶች የግብርና ግብዓቶችን የሚያቀርቡ በግብርና ሥራ ላይ የተሰማሩ የአካባቢው ነዋሪዎች ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይጠበቃል። ፓርኩ በማር፣ በስጋ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በዘይትና በጥራጥሬ ማቀነባበር የሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚገቡበት በመሆኑ አርሶ አደሮች ለአምራቾቹ ግብዓት በማቅረብ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ አቶ ጌታቸው ተናግረዋል። ‹‹ፓርኩ ለአካባቢው ማሕበረሰብ ብዙ የሥራ እድሎችን ፈጥሯል። የአካባቢው ሕብረተሰብ ለፓርኩ የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማው ተከታታይ ሥልጠናዎችና የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶች ተሰጥተዋል›› ብለዋል።

በቀጣይ ጊዜያት ከ80 እስከ 120 አምራቾች ወደ ፓርኩ ይገባሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ የጠቆሙት አቶ ጌታቸው፣ የልማት አጋሮችና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የኢንዱስትሪ ፓርኩን ወደ ሥራ ለማስገባት ለሚደረገው ጥረት ዘርፈ ብዙ እገዛዎችን እንዳደረጉና በዚህ ረገድ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢንዱትሪ ልማት ተቋም (UNIDO) እና አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ተጠቃሽ እንደሆኑ ተናግረዋል።

ባለሀብቶች ወደ ፓርኩ ገብተው ለመሰማራት ፍላጎት እያሳዩ እንደሆነ የተናገሩት አቶ መሐመድ ሐሰን፣ እስካሁን ድረስ ከስድስት ኩባንያዎች ጋር የመግባቢያ ስምምነቶች እንደተፈረሙም ገልጸዋል። አምራቾቹም በስጋ ማቀነባበሪያ፣ በአቮካዶ ዘይት፣ በማር ምርትና በምግብ ዘይት ማምረት ላይ ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸው ናቸው። ሸካ ሞርዲ የተባለ የማር ማቀነባበሪያ ድርጅት ደግሞ የሙከራ ምርት ጀምሯል። ይሁን እንጂ ኢንዱስትሪ ፓርኩ ባለሀብቶችን ለመቀበል ዝግጁ ቢሆንም ባለሀብቶቹ ከፋይናንስ አቅርቦት ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሟቸው ቢሮክራሲያዊ መሰናክሎች በፍጥነት ሥራ እንዳይጀምሩ ጫና እንደፈጠረባቸውም አቶ መሐመድ ተናግረዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ለሀገራዊ የኢንቨስትመንት እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ የማበርከት ግብ አላቸው። በዚህ ረገድ የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክም ለሀገራዊ ኢንቨስትመንት ዘርፈ ብዙ ሚና እንደሚኖረው አቶ መሐመድ ይናገራሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፣ ኢንዱስትሪ ፓርኩ አምራቾችን በመሳብ የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር ያደርጋል። ፓርኩ ብዙ የሥራ እድል በመፍጠር ከሚኖረው ሚና በተጨማሪ ግብርናውን በማዘመንና ምርቱን በማሳደግ ምርት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ በማቅረብ የአቅርቦትና የውጭ ምንዛሬ ችግሮችን ለማቃለል ያግዛል። የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖርም ያደርጋል። ለአርሶ አደሩ የገበያ ትስስሩን ቀላል በማድረግ ተጠቃሚነቱ እንዲያድግ ያስችላል።

የአገሪቱን የምጣኔ ሀብት መዋቅር ከእርሻ መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያግዙ በርካታ መልካም አጋጣሚዎችና እድሎች አሉ። ይሁን እንጂ እነዚህን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት የተከናወኑ ተግባራት ሀገሪቱ ካላት አቅምና ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም። ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ ያላትን አቅም በመጠቀምና ከዚሁ ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የምታደርገውን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግር ለማሳካት አምራች ዘርፉ አሁን ካለው አፈፃፀም በብዙ እጥፍ እንዲጨምርና እንዲሻሻል ማድረግ ያስፈልጋል።

የአምራች ዘርፉ እድገት ሊሻሻል የሚችለው ከኢንቨስትመንት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ነው። የኢንዱስትሪ ፓርኮች ደግሞ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ተግባራዊ በማድረግ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ናቸው። ስለሆነም መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግሩን ለማሳካት የኢንዱትሪ ፓርኮችን አፈፃፀም ማሻሻል ይገባል። ይህም ባለሀብቶች ወደ ፓርኮቹ ገብተው ለማምረት የሚያስችሏቸውን የመሰረተ ልማት ግብዓቶች፣ የሰለጠነ የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅርቦት ማሟላትን እንደሚያካትት ሊታወቅ ይገባል።

# ጎሜ

# ሰኔ...ሰኔን ስምን?

«አቤት ዝናቡ ሀምሌን መስሎ የለ እንዴ?። ዘንድሮ ደግሞ ለየት ያለ ነው ፤ ገና ከአመጣጡ ያስፈራል። ኧረ ! ጎርፉ የህጻናትን ህይወት እየቀጠፈ ነው፤ አደጋው በዝቷል... » ይላሉ በምንጓዝበት ታክሲ ውስጥ ከጎኔ የተቀመጡት አዛውንት። ጉዳዩ የእኔም ስጋት ጭምር በመሆኑ የጨዋታው አካል ላለመሆን አልፈለኩም። «እውነት ነው» ስል ሀሳባቸውን ጭንቅላቴን ነቅነቅ አድርጌ አረጋገጥኩላቸው ። ደግሞም እኮ ዝናቡ ከዳር እስከ ዳር ጠንከር ብሏል።ያው እንግዲህ ያየነው የአዲስ አበባን አይደል፤ ጨዋታችንም እዛው አካባቢ ነው። ከወደየክልሉ ከአየር ትንበያ መስሪያ ቤቱ ውጪ ማረጋገጫ የለንም።

«ሞቴን በሀምሌ ጨለማ አያድርገው» ይሉ ነበር አያቴ። የሀምሌን ወር በጣም አድርገው ይፈሩታል። ቀልባቸው ሀምሌን አይወደውም፤ ቢሆንም እንኳን ከክረምቱ ነሀሴ ይሻላቸዋል። ክረምቱ ከመግባቱ በፊት ቀለባቸውን፣ ጉዳያቸውን ሁሉ አጠናቀው በሀምሌ በር ዘግተው ይቀመጡ ነበር። ቀኑ ብራ የሆነ ሰዓት ሮጥ ብለው የቤተክርስቲያን ደጅ ይረግጡ ይሆናል እንጂ በጭራሽ ወሩን ለስራ አይመኙትም። ሞታቸውም በሀምሌ ዶፍ እንዳይሆን የሚማጸኑትም ቀባሪ እንዳይመረር ፣ በድናቸው ጎርፍ በሞላው ጉድጓድ ውስጥ እንዳይወድቅም አይደል!።

እንኳንስ በህይወት እያሉ በአይናቸው እያዩ በዝናብ ምንም ማድረግ አይፈልጉም። ክፉውን እንዲያርቀው ነው ጸሎታቸው። እናም ሰውንም ሲመርቁ ሁሉም ነገር በበጋ በፀሀይ እንዲሆን በመመኘት ነው። « የሀምሌ ዝናብ ቡጢውን ያሳርፍብናል፤ ወንዝ የማያሻግር ክፉ ወር ነው። እንኳን ሰው የመስቀል ወፍ እንኳን የክረምት ቀለቧን በበጋ ሰብስባ በጎጆዋ ትከትታለች» ይሉ ነበር። ዘመድ አዝማድ የሚጠየቀው ወንዝ ተሻግሮ የሚኬደው ከመስቀል ወዲያ መሆኑን ደጋግመው የነገሩኝን አስታውሳለሁ። ዛሬ ዛሬ «ሰው ከቤቱ ተፈናቀለ፤ ተራበ ፣ እዚህም እዚያም ሰዎች በአሸባሪዎች ተገደሉ፤ በአሰቃቂ ሁኔታ ታረዱ...»የሚለውን ቢሰሙማ ሰማይ የተደፋባቸው ያህል ጭንቀታቸውን ያሳዩ ነበር። ምክንያቱም ለመኖራቸው ሳይሆን ለሞታቸው ይማጸኑ ነበርና ነው። ምን በሀምሌ ጨለማ ብቻ ከዛ የከፋ አለ ቢባሉም ይህን ከምሰማና ከማይ ሞቴን ይሉ እንደነበር እገምታለሁ። ትንሽ አሰቃቂ የሆነ ነገር እንኳን ሲሰሙ «ኧረ ! የሰይጣን ጆሮ አይስማው» ነው የጨዋታ ሁሉ ማሳረጊያቸው ።

የታክሲው ላይ ጨዋታ የሁላችንንም አንደበት አፍታታው አይደል? እኔም አያቴን ከነምክራቸው፣ ፍርሀትና ስጋታቸው ሁሉ በምልሰት አስታወስኳቸው። ምነው በዚህ ዘመን ቢኖሩ ነበር ስል ተመኘሁ። የክረምቱን ማየል እንዲያዩ ሳይሆን በክረምቱ ከቤት ንብረቱ የተፈናቀለውን፣ በየቦታው የሚሞተውን ህጻን አዋቂ፤ ሴት ወንድ ፤አዛውንት ፣ የሀይማኖት አባት ሁሉ ሲሞት፣ ሲቃጠል፣ ሲታረድ ፤ ቤተክርስቲያን መስጊዱ ሲቃጠል ሲያዩና ሲሰሙ ምን ይሉ እንደነበር ለመስማት ነው። ብቻ የእሳቸው ጸሎት «ክፉ አታሳየኝ» ነበርና የአሸባሪውን ሸኔ፣ የሴረኛውን ሕወሓት ግፍ የሌላውንም ክፉ ክፉውን ሳያዩ በጊዜ አሸለቡ።

እናት አንጀቷ እያረረ በልጆቿ ስቃይ ስትተክን፤ የቤተሰብ አስከሬን በእሳት ጋይቶ አመድ ሲሆን፤ ከልጅነት እስከ እውቀት ያፈሩት ንብረት ወደ ፍርስራሽነት ተቀይሮ ትዝታ ሲሆን ይህን ሁሉ ጉድና መከራ ቢሰሙ ከሟቾቹ ቀድመው ጉድጓድ ያስምሱ ነበር። ያውስ ሟቾች የሚቀብራቸው ካገኙ ማለቴ ነው!። የከፋቱ ጥግ እንኳን ለእሳቸው እኛም ለሰማነው ጉድ! አሰኝቶናል አይደል!?። ምነው ጆሮ ወሬ ጠገብኩ ብሎ ቢያስቀርልን ኖሮ።

የክረምቱ ነገር ስንቱን አስታወሰን፤ የድሮ ክረምትም እንዲሁ ቀደም ብሎ እየገባ በጋው ሁሉ ዝናብ ይሆን ነበር አሉ። ያኔ ታዲያ ሁሉ ነገር ጥጋብ ነበር። ከብቱ ሳር እንደልቡ ይግጣል። ውሃውም ሞልቷል። በበልጉ እህል ይመረታል... በዛው ልክ ኑሮው ጥጋብ ነው ምን ጠፍቶ ሁሉ ሞልቶ። ዘንድሮ ግን ጊዜው ተቀየረ እንዴ ሀምሌ በሰኔ ላይ ቀድሞ የገባ ይመስላል። የሰኔው ዝናብ እጅግ ከበድ ብሏል። በጸሀይ ተቃጠልን፣ ነደድን፣ ሙቀቱ መተንፋስ እስኪያቅተን ብለን ዣንጥላ መጎተት ጀምረን ነበር። ሌሊት ሳይቀር « ልብስ ቀንሱ» የጨዋታ ማድመቂያ አልነበር። ምን ይሄ ብቻ የቧንቧ ውሃ በሳምንት፣ በአስራ አምስት ቀን፤ አንዳንዶች እንዳሉት እስከወር ድረስ ውሀ የውሀ ሽታ የሆነበትም ምክንያት አንዱ ድርቁ እኮ ነው።

እነቦረናን ሶማሌ ክልልም የነበረውን ድርቅ አንረሳም ስንቱ የቦረና በሬ በውሃ እጦት፣ በመኖ አለመኖር በድርቁ ረግፏል፤ አርብቶ አደሩ የቀሩት ከብቶቹ ከእጁ ሳያልቁ እየተንገዳገዱ የሚራመዱ እንስሳቱን ይዞ ተሰዷል። ያ ሁሉ አለፈ ተመስገን ነው። አሁን ከዳር እዳር ዝናብ መጥቷል። መሬቱ መረስረስ ቀጥሏል። አብሮት ግን ስጋቱ አይሏል። ጎርፍ አደጋ ሆኖ ፊት ለፊት ተደቅኗል። ይሄ ጥንቃቄ ይፈልጋል አይደል?። አዎ! ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አውቀን ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ መያዝ አለብን። እውነት ነው፤ የሚያስማማ ሀሳብ በራሳችን እራሳችን ተነጋግረን ተስማምተን ችግሩን ልንፈታ እንችላለን። ቦይ ሰርተን ጎርፉ እንዲሄድ እናደርጋለን... ሌላም ሌላም። ይሄ የሚቻል አይደል? ይቻላል እንጂ ለምን አይቻልም። በእርግጥ የዝናብ መክበድ ሊያጋጥም ይችላል። የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት ምን ልናደግ እንችላለን በእኛ አቅም አስቀድሞ የአደጋ ስጋት የሆኑትን ስፍራዎች መለየት፣ በምን መልኩ ችግሩን መቋቋም እንደምንችል መነጋገርና መስራት ይገባናል። ሌላውን ደግሞ የሚመለከተው ትኩረት እንዲሰጠው ጉዳዩን ማሳሰብ አይደል?።

ከጎኔ የተቀመጠችው ወይዘሮ አልፎ አልፎ ከእሷ ደግሞም ከእኔ የሚወጡትን የመወያያ ጉዳዮች ለብቻዋ ራሷን ካጫወተች በኋላ መሰለኝ እንዲህ ስትል በመሃላችን የነበረውን ዝምታ ሰበረች። «ይሄ የተፈጥሮ አደጋ ሁላችንንም አሳሰበን መሰለኝ፤ እኔን ያሳሰበኝ ግን ከዚህ በላይ ሰው ሰራሽ አደጋዎች ናቸው አለች» የቱ? ስል ጥያቄ አንስቼ ወሬውን አራዘምኩ ። ምንም ሳትፈራ ፊቷን ጨምደድ ፈካ እያደረገች አሁን እኮ ሁሉም ነገር እንደልብ ይወራል፤ መፍትሄ ባይኖርም ችግሩ ይገለጻል። ማን ማንን ይፈራል? ማንን ያከብራል? ምክንያቱም የመናገር ዲሞክራሲ አለና ነዋ!። እሷም መብቷን ተጠቅማ ነው መሰል ቀጠለች።

«ሰኔን ጠብቀው የክረምቱን መግባት አስበው ህዝብን የሚያፈናቅሉ፤ ዜጎችን የሚጨፈጭፉ፤ ቤትና ንብረት የሚያቃጥሉ የውስጥና የውጪ ሀይሎች ሴራ ነው የሚያሳስበኝ። አይገርምሽም! ከለውጡ ጀምሮ ብዙ አስፈሪና ጭካኔ የተሞላቸው አሰቃቂ ክስተቶች በሀገራችን ታይተዋል። ድሮ ‹ሰኔና ሰኞ› ሲባል እሰማ ነበር። ሰኔና ሰኞ ሲገጣጠሙ መልካም ነገር አይገጥምም የሚል አባባል ። አሁን አሁን ግን ሰኔና ሰኞ ሲገጥም ሳይሆን ሰኔ...ሰኔ ሲመጣ ጀምሮ መሳቀቅ እጀምራለሁ፤ ክረምቱ ምን ይዞብን ይመጣ ይሆን እያልኩ አስባለሁ። ዘንድሮ ደግሞ እልቂቱ የትኛው ቦታ ላይ ይሆን በማንነቱ የተፈረደበት? የየትኛው እምነት ተከታዮች ይሆኑ የሚጨፈጨፉት እያልኩ ማውጣት ማውረድ፣ ጆሮ ጥሎ ማድመጥ ስራዬ ሆኗል» አለች። ቀና ብላ አምላኳን እባክህ እየን፣ ተመልከተን፤ በቃ በለን! የምትል በሚመስል ተማጽኖ።

ወይዘሮዋ ረጅም ትንፋሽ፣ ተስፋ የቆረጠ ድምጸት ካወጣች በኋላ መለስ ብላ ያለፈውን እያስታወሰች መናገሯን ቀጠለች። «ትዝ ይልሻል?»አለች « ሰኔ 16 ቀን ህዝቡ ባገኘው ለውጥ ተደስቶ ለጠቅላይ ሚንስትሩ እውቅና እና ምስጋና ለማቅረብ መስቀል አደባባይ የተገኘ እለት» ራሴን ነቀነቅኩ። የደስታውም የችግሩም አካል ነበርኳ። «ደስታው እኮ በሀዘን፣ በድንጋጤ፣ በጭንቀት እንዲደመደም ነው የተደረገው። ጠቅላይ ሚንስትሩ ላይ የተደረገው የመግደል ሙከራ ተሳክቶ ቢሆን ኖሮ ብለሽ አስበሽዋል ሀገር ይተራመስ ነበር፤ የጎበዝ አለቃ ሁሉ ከየቦታው ሊፈጠር ይችል ነበር፤ ብቻ ፈጣሪ ሁሉንም ነገር ኩም አደረገው። ያኔ የተጀመረው የሰኔ ትርምስ ዛሬም ድረስ ዘልቋል» ስትል ስጋት በሰፈነበት ድምፅ አጉረመረመች። ቀጠለች፤ «ዓመት ዓመት ቆጥሮ በየክረምቱ ህዝብና ሀገርን ማሸበር ነው። በሰኔ 16 በዓመቱ ሰኔ 15 ቀን ደግሞ የመከላከያ ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም፣ የአማራ ክልል ከፍተኛ አመራሮች የመሳሰሉ የሀገር ባለውለተኛዎች በአሰቃቂ ሁኔታ ተገደሉ። ይሄ አስደንጋጭም አሳዛኝም ክስተት ነበር። በዛው ግን ግድያው አልቆመም አሁን ድረስ የውስጥ አሸባሪዎች ከኢትዮጵያ ጠል የውጪ ሀይሎች ጋር ሆነው ሀገር የማተራመስ ህዝብ የማስጨነቅና የማሰቃየት ስራቸውን ቀጥለዋል። ሰማይና ምድሩን በደም እያራጩ አሰቃቂ ሞትን ሁሉ አሳይተዋል።» እያለች በምልሰት የየዓመቱን የሰኔን ወር አሰቃቂ ጊዜያት ሁሉ አስቃኘችኝ።

ጋዜጠኛ ትሆን እንዴ? ዜናውን ከነጊዜው ታስታውሰኝ ቀጠለች ። ግን እኮ አሁን ሁሉ ነገር በእጅ በደጅ አይደል፤ የሚደበቅና የሚረሳ ነገር የለም። ጎግል ጎልጉሎ መረጃውን ሁሉ እጃችን ላይ ያደርሰዋል። እና ሁሉም ጋዜጠኛ ባይሆን ይገረማል። ምን ጋዜጠኛ ብቻ ፖለቲከኛም ሆኗል እንጂ። ወዲያው በአንድ ወቅት ከመገናኛ ብዙሀን የሰማሁት ትዝ አለኝ። «ሁሉም ፖለቲከኛ ሆኗል። ሁሉም አራት ኪሎ ገብቷል። ስለዚህ ‹ሰዎች› መገኘት ባለባቸው በቤተክርስቲያንና በመስጊድ ጸሎተኛ ጠፍቷል፤ በየቤተ መጽሀፍቱ አንባቢ ርቋል፤ ሁሉም ከሙያው ተፈናቅሏል» የሚል ነበር።

«እንዳው በሞቴ አሁን በኢትዮጵያ የሚሰማው እልቂት ሁሉ ታሪክ ይቅር የሚለው ይመስልሻል?» ሀሳቧን በጥያቄ አስደግፋ አቀረበችልኝ እንደ ድግስ ቡፌ ምርጫውን ለእኔ ትታ። መልስ አልሰጠሁም ግን ማን ጠብቆኝ «እኔ በበኩሌ» ብላ የበኩሏን ስሜት እንዲህ ስትል አጋራችኝ። «ሌላ የሰማዕታት ሀውልት እንድናቆም የሚያደርግ ነው። ከነበረው ከጠላነው፣ ከአወገዝነው ስርዓት፣ ነበር ካልነው ጭፍጨፋ አልተማርንም። እንዳውም ባይብስ ብቻ ይሄን ሁሉ ያስታወሰን ክረምቱ ነው» ብላ ዞር ዞር ብላ አካባቢዋን በአይኗ ቃኘች።

ጨዋታውን ያደመጡት አዛውንቷ መርካቶ ደርሰን ከታክሲው ሳንወርድ ያሰቡትን ሀሳብ ጣል ጣል አደረጉ። እውነታቸውን ነው «የሰው በልቶ...»የሚል የሀበሻ ተረት አለ አይደል? እንዲያ በሉት። «ኧረ ምኑ ቅጡ » ሲሉ የጨዋታ ማሞቂያ አፋቸውን እያሟሹና እያሻሹ ነው የጀመሩት «ያ ተወዳጅ የኦሮምኛ ዘፋኙ ስሙ ማን ነበር? » እያሉ ለማስታወስ የታክሲውን ጣሪያ ጣሪያ ሲያዩ ወይዘሮዋ ፈጠን ብላ «ሀጫሉ» ብላ ከተጓዙበት የሀሳብ መንገድ መለሰቻቸው።«አዎ! ሀጫሉ። እሱም እኮ እንዲሁ በክረምት ነው የገደሉት የሟቾች ደም በዝናብ ይታጠባል፣ በጎርፍ ይወሰዳል፣ አይታይም ብለው ይሆን? እንጃ ብቻ! አሁንም እኮ ሀገር የሚያተራምሱ ደም የሚያፈሱ በማንነቱ የሚጨፈጭፉ አሸባሪዎች በርክተዋል። እዚያ ማዶ እዚህም ማዶ ጩኸቱ በርክቷል። ሟች በዝቶ ቀባሪ ጠፍቷል። ነፍሰጡርን ገዳይ፣ ህጻናት አራጅ ‹ጀግና› ተስፋፍቷል» የችግር ክምር አስታወሱን። በዚህም አልረኩም መሰለኝ «ኧረ እንዳው በሞቴ » አሉ አንድ ጊዜ ጆሮ ሰጥተን እንድናደምጣቸው በመማጸን።

ከፊት ከኋላ የታክሲው ተሳፋሪዎችም የጨነቃቸውና መልስ ያጡለት ጉዳይ በመነሳቱ ደስ ብሏቸዋል። በሰፊው ቦታም ባይሆን በጠባቧ መድረክ መተንፈስ አስችሏቸዋል። እናም አዛውንቷ «አሁን ወለጋ ላይ በማንነታቸው የተጨፈጨፉት ንጹሀን ሰዎች አይደሉም። ሸኔ ብሎ የክፉዎች ክፉ የጨካኞች ጨካኝ ይህን ድርጊት ሲፈጽም እሰይ! አበጀህ! ጎሽ የእኔ ጀግና የሚለው የሚያገኝ እየመሰለው ይሆን እንዴ! ከሆነ ተሳስቷል። አሰላፊዎቹ ከህዝብ ልብ እያወጡት፣ አክ እንትፍ! እየተባለ መሆኑን ማን በነገረው። ህዝብን ጨፍጭፎ ለህዝብ ቆሚያለሁ፤ ህዝብን አደህይቶ ለልማት አለሁ። ሀገርን አውድሞ ሀገሬ ቢል የቁም ቀባሪ ነው። ከአይዞህ ባይ ቢደጎምም የጊዜ ጉዳይ ነው። አያዋጡትም፤ ግብጥም ብትሆን በውስጥ ጉዳይ ሲተራመሱ ህዳሴ ግድቡ ይስተጓጎላል ከሚል ተስፋ ይመስለኛል። ሞኝ በያት አይሆንላትም! ኢትዮጵያውያን ማለት «የነብርን ጅራት አይዙ ከያዙም አይለቁ» መሆናቸውን ባትረዳው ነው። ምንም ነገር ቢመጣ የአባይ ጉዳይ በቃ የህልውና ጉዳይ ነው። እንዳይመስላት የሚቆም ነገር የለም» እያሉ ቀጠሉ።

«የአውሮፓ ህብረት የምትሉት ግብጽ የአባይን ውሀ የመጠቀም ታሪካዊ መብት አላት ...ምናም» ሲል ነበር ሰሞኑን በዜና እንደሰማሁት አሄ ምንም ቢሉ መብቱማ የእኛው ነው 85 በመቶ ለምናመነጨው፤ እሷንስ ቢሆን መች ከለከልን እንዳው እናንተ ይቅርባችሁ ሁሉ ለእኔ ለእኔ ሆኖ እንጂ!» ጨዋታው ደርቷል መውረጃችን ተቃርቧል። ባልናገርም ሁሉም በስሌት ነው፤ ሰኔ ሰኔ እየተጠበቀ። ብልጥ ይሄኔ ነው ሰኔን ለጦርነት ድግስ ሳይሆን ለእርሻ የሚያውላት እያልኩ እኔም የምናብ ጉዞዬን ገታሁ ።

**የታክሲው ላይ ጨዋታ የሁላችንንም አንደበት አፍታታው አይደል? እኔም አያቴን ከነምክራቸው፣ ፍርሀትና ስጋታቸው ሁሉ በምልሰት አስታወስኳቸው። ምነው በዚህ ዘመን ቢኖሩ ነበር ስል ተመኘሁ። የክረምቱን ማየል እንዲያዩ ሳይሆን በክረምቱ ከቤት ንብረቱ የተፈናቀለውን፣ በየቦታው የሚሞተውን ህጻን አዋቂ፤ ሴት ወንድ ፤አዛውንት ፣ የሀይማኖት አባት ሁሉ ሲሞት፣ ሲቃጠል፣ ሲታረድ ፤ ቤተክርስቲያን መስጊዱ ሲቃጠል ሲያዩና ሲሰሙ ምን ይሉ እንደነበር ለመስማት ነው። ብቻ የእሳቸው ጸሎት «ክፉ አታሳየኝ» ነበርና የአሸባሪውን ሸኔ፣ የሴረኛውን ህወሓት ግፍ የሌላውንም ክፉ ክፉውን ሳያየ በጊዜ አሸለቡ።**

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## ትንታጉ ብዕረኛ

ተገኝ ብሩ

ወደ ጥበብ ገበታ ቀርቦ መቋደስ የማይፈልግ ፤በጥበብ ትሩፋት ዘልቆ ነፍሱን ማደስ የማይሻ የሰው ልጅ መኖሩ ያጠራጥራል። ጥበብ በአንድ ወይም በሌላ መልክ በሰዎች ሁለንተናዊ ህይወት ውስጥ ይገለጣል። ሰዎች እራሳቸውን የሚገልጡበት፣ባህልና ማንነታቸውን የሚያስውቡበት ስብዕናቸውን የሚያንፁበትና አኗኗራቸው የሚያንፀባርቁበት ልዩ መድረክም ነው። ታዲያ ጥበብ ጥበበኛን ሁሉ በእኩል አትጣራም። ወደ መግቢያ በርዋ ለሚቀርብ ሁሉ በእኩል ምላሽ አትሰጥም።

ጥበብ በራስዋ ሚስጥር ናትና በራስዋ መንገድ ሰዎችን በተለያየ መንገድ ወደራሷ ትጣራለች። ጥበብ ለጥሪዋ ምላሽ የሚሰጡ ዕድለኞችን ትመርጣለች። አንዳንዱን በሯዋን በሰፊው ከፍታ ከማዕድዋ ይቋደስ ዘንድ ገራገር ትሆንለታለች። ቤተኛዋ ይሆን ዘንድ ፈቅዳ ያላትን ሁሉ እንካ ብላ ከበረከትዋ ይቋደስ ዘንድ ትፈቅድለታለች።በዛሬ የዘመን ጥበብ ገፃችን እራሱን ከጥበብ ጋር ካስታረቀ ወጣት የብዕር ሰው ስራዎችና ተሞክሮው ለማየት ወደናል መልካም ንባብ።

### ለጥበብ ጥሪ የተሰጠ ምላሽ


ጥበብ ወጣቱ ደራሲ ዘላለም ከሚወደው የቀለም ትምህርቱን አሽፍታ የአንተ መክሊት እኔ ጋር የተቃረበ ነው ብላ ግብዣ አቀረበችለትና ተቀላቀላት። በትምህርት ቤት ህይወቱ በጥሩ ውጤት ከሚታወቁ ተማሪዎች አንዱ ነበር። ወደኋላ ላይ ግን ውስጡ አንድ ጥያቄ መፈጠር ጀመረ። እኔ የተፈጠርኩት እዚህ ምድር ላይ ለምን አላማ ነው?ማሳካት የምፈልገው ምንድነው? ውስጤ ወዴትኛው አቅጣጫ ነው መሄድ የሚፈልገው? የሚል። ታዲያ በትምህርት ቤት ቆይታው ያዘወትረው የነበረው የምንባብ ፍቅርና በትምህርት ቤት ኪነ ጥበብ ክበብ ይሳተፍበት ወደነበረው ጥበባዊ ጉዳይ ላይ የእሱ ስሜት ስስ መሆኑን ተረዳ። ከትምህርቱ ጎን ለጎን አዘውትሮ ኪነጥበባዊ መድረኮች ላይ መገኘትና እራሱም መሳተፍ ጀመረ።

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የኢንጅነሪንግ ተማሪ ሆኖ በተመደበ ሰዓት ግን ከራሱ ጋር መከረ። እናም አንድ የራሱ የሆነ ፍልስፍና ነበረውና እርሱን መኖር ፈለገ። "የሰው ልጅ በምድር ላይ የሚገኘው አንድ ጊዜ ነውና ድንቅ ሰውነቱን በሚወደው ሙያ ላይ ማሳረፍ አለበት" የሚል መርህ ለእርሱ ተገለጠ። የሚወደው ኪነጥበባዊ ጉዳይ ላይ መሳተፍ የጥበብ ሰው መሆንን ነበርና በዋናነት እሱን በትርፍ ሰዓቴን ደግሞ የቀለም ትምህርቱን መማር አለብኝ ብሎ ወሰነ። ያ ውሳኔው ዛሬ ላይ የሚደሰትበትና ፍሬ ያፈራለት የሚፈልገው ላይ መኖር ያስቻለው ወደሚወደውም ያስጠጋው ሆነለት፤ደራሲ ወጣት ዘላለም።

በ2007 የጀመረው እርሱ ጋር ያለው ጥልቅ የጥበብ ፍቅርና ልዩ ተሰጥኦ በትምህርትና ልምድ አዳብሮ መፅሀፍትን በመፃፍ የጀመረው ጉዞው ዛሬ ላይ 15 መፅሀፍ ፅፎ ለህትመት አብቅቷል። እርሱ በብዕሩ ፍቅርን ሰብኳል፣ በፅሁፎቹ አንድነትን ነግሯል፣በጥበብ አዋዝቶ ማህበራዊ ህፀፆች ይታረሙ ዘንድ ጠቁሟል። ብዙዎች በራሱ የአፃፃፍ ስልቱ የሚደነቁበት ደራሲ ዘላለም የሳጥን ወርቅ ማህበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች እያነሳ የግል ፍልስፍናውንና ልዩ ምልከታውን በማይነጥፈው ብዕሩ አንፀባርቋል።

### የደራሲው ስራዎች

ሰኔ 18 ቅዳሜ 4 ኪሎ በሚገኘው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የመሰብሰቢ አዳራሽ የደራሲ ዘላለም የሳጥን ወርቅ 15ኛ መፅሀፍ የሆነው "የነፍስ ዜማ" የተሰኘ መፅሀፍ ታዋቂ የኪነ-ጥበብ ሰዎች በተገኙበት ተመርቋል። በምሽት ትምህርቱን ቀን ላይ ደግሞ ጥበባዊ መሻቱን ለማሳካት ሲባትን የነበረው ዘላለም




ከሌሎች ጋር በመሆን ሶስት የተለያዩ የግጥምና አጫጭር ልቦለድ ስራዎቹን አሳትሞ ወደ ድርሰት ሙያ ተቀላቀለ።

የራሱ ወጥ ስራ ሰርቶ ሌተቀን ጥረት ማድረጉን ቀጠለ በመጨረሻም ከአንድ በቅርቡ ካለው ለፅሁፍ ዝግጅት እዲሆነው የተበረከተለት ኮምፒዩተር መግዣ ገንዘብ ቀድሞ ያዘጋጀው መፅሀፉን ሊያሳትምበት ወሰነና "እፀ ሳቤቅ" የተሰኘ የራሱን ስራ ለህትመት አበቃ። በዚህም ብዙዎች በጎ አስተያየትን ሰጡት ያሳተመው ህትመት ቁጥሩ የበዛም ባይሆን በሁለት ወር ውስጥ ተጠናቆ ባየ ጊዜ ለራሱ ብርታት አገኘ። የሚወደውና የሚፈልገው ስራ መፃፍ በኪነጥበቡ ዓለም የራሱን አበርክቶ አንካችሁ ማለት ነበርና መንገዱን ተያያዘው በትጋት መፃፍ ቀጠለ።

ደራሲው ባለፉት 7 ዓመታት ውስጥ ከፃፋቸውና አንባቢ ጋር ካደረሳቸው መፅሀፎች ውስጥ እፀ ሳቤቅ፣ እፀጳጦስ አሁን፣እፀሲና፣ሊቶስጥራ፣ብኤልዘቡል፣ሽርፍራፊ ልቦች፣ፍካትና ንጋት፣የህይወት ዋጋ፣ፊትና ኋላ፣ አዳፋ ነብሶች፣እንደ ፍቅር፣እውነት፣ ሰውነት፣አሁንና የመጨረሻ መፅሀፉ የነፍስ ዜማ የተሰኙት ተጠቃሾች ናቸው።

በተለይም የማህበረሰባችን ልዩ ልዩ መልኮች በግጥም በወግ በአጭርና በረጅም ልቦለዶቹ እያፈራረቀ በመፅሀፎቹ ለአንባቢያን የሚያበቃው ወጣቱ ደራሲ ዘላለም፤ በራሱ የአፃፃፍ ስልት በተለየ የአተራረክ ዘይቤ በሚያቀርባቸው የመፅሀፍ ጽሁፎቹ ይታወቃል።

በመፅሀፎቹ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን እያነሳ በልዩ የአተራረክ ስልት በውብ ቃላት ከሽኖ የሚያቀርበው ደራሲ ዘላለም ስለ ፍቅር፣ስለ አገር፣ስለ እናትና አባት፣ስለቤተሰብ፣ እና ማህበረሰብ፣ስለ ባህልና እምነት እውነት እያራረቀ በተለያዩ ታኮች አሳይቶናል።

### ስለደራሲው ምን ተባለ

ደራሲ ዘላለም የሳጥን ወርቅ "የነፍስ ዜማ" የተሰኘው መፅሀፉ ባለፈው ሳምት ባስመረቀበት ወቅት በአገራች በስነፅሁፍ ተፅዕኖ መፍጠር የቻሉ የኪነጥበብ ባለሙያዎች ተገኝተው ነበር። በዚሁ ደማቅ የምረቃ ስነ ስረዓት ላይ የደራሲው ቀደምት ስራዎችና ስነ ፅሁፋዊ ይዘታቸው በተመለከተ ሀሳብ ሰጥተው ነበር።

የመርሀ ግብሩ የክብር እንግዳ የነበረው መምህር ደራሲና ፀሀፊ ተውኔት አያልነህ ሙላቱ የደራሲው ስራዎች በተመለከተ በመድረኩ ላይ አስተያየት ሰጥቶ ነበር። ወጣቶች ከንባብ ርቀው ጊዜያቸውን አልባሌ ቦታ ላይ በማሳለፍ አሉታዊ ተፅዕኖ እየፈጠሩ ባሉበት በዚህ ሰዓት የደራሲ ዘላለም አይነት ትጉህና በብዕሩ

> "የሰው ልጅ በምድር ላይ የሚገኘው አንድ ጊዜ ነውና ድንቅ ሰውነቱን በሚወደው ሙያ ላይ ማሳረፍ አለበት"

ሰዎችን ለማስተማርና ማህበረሰቡን ለማቅናት እንዲሁም በአስተሳሰብ ለመለወጥ የሚጥር ወጣት መገኘቱ ተስፋ ያለመልማል በማለት ስለ ወጣቱ ደራሲ ዘላለም ያለውን አስተያየት ሰቷል።

በደራሲው የአፃፃፍ ስልት እጅጉን የሚደነቅ መሆኑን የገለጸው ፀሀፊ ተውኔት አያልነህ ሙላቱ "ደራሲ ዘላለም በድርሰቱ ውስጥ የሚጠቀምባቸው ቃላት ውበትና የአገላለፅ ብስለት ጥበባዊ በመሆኑ ይማርካል፤በተለይ አካባቢና ተፈጥሮን በተለየ መልክ የሚያሳይበት ስዕላዊ ቃላቱ ይለዩብኛል።" በማለት የደራሲው ስራዎች የተመለከቱበት አስተያየታቸውን አጋርቷል። በተለይም መፃፍ ቀርቶ ማንበብ ብዙም ልምድ የሌለው ማህበረሰብ ውስጥ ተገኝቶ በዓመት ሁለት ደረጃቸውን የጠበቁና ስነ ፅሁፋዊ ፋይዳው ከፍ ያለ መጽሀፍ ፅፎ ለአንባቢ ማድረስ እጅጉን ከባድ መሆኑን የገለፀው ፀሀፊ ተውኔት አያልነህ ሙላቱ ደራሲ ዘላለም በ7 ዓመታት ውስጥ 15 መፅሀፍን ለንባብ ማድረሱ ለብዙዎች ትምህርት እንደሚሰጥና ጊዜን መጠቀም ዋጋ እንዳለው አመላካች መሆኑን ጠቅሷል።

መጽሀፍ ምርቃት ስነ ስረዓት ላይ ደራሲው ከዚያ በፊት የፃፋቸው መጽሀፍት በተመለከተ አስተያየት ከሰጡ ባለሙያዎች አንዷ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ስራ አስኪያጅ የሆነችው ደራሲት የዝና ወርቁ የደራሲው ቀደምት ስራዎችና አዲሱ መፅሀፍ በተመለከተ እንዲህ ብላለች። ደራሲ ዘላለም ከእድሜው በላይ ከፍ ያለ ስራዎችን መስራት ያስቻለው ታላላቅ ከሆኑ ሰዎች ዝቅ ብሎ ምክር መቀበሉና በጥሩ ስነምግባር ከሰዎች ጋር ተግባብቶ ሙያው ካላቸው ሰዎች መቅሰም በመቻሉ እንደሆነ አስረድታለች።

በፅሁፎቹ ውስጥ የሚያነሳቸው ርዕሰ ጉዳዮች እደምትደነቅና ጉዳዮቹን የሚገልፅበት መንገድ ልዩ መሆኑን የምትናገረው ደራሲት የዝና፤ በእርሱ እድሜ ያሉ ወጣቶች እጅጉን ሊማሩበት እንደሚገባ ገልፃለች።በገፀባህሪያቱ ውስጥ የሚስላቸው ሴቶች ለሌሎች አርአያ የሚሆኑና ደራሲውም ለሴት ልጅ ያለው አመለካከት እጅጉን የተቃና መሆኑን አመላካች ነው ያለችው ደራሲት የዝና የማህበረሰባችንን ባህልና ጥሩ ገፅታን በመገንባትም ደራሲው በብዕሩ የራሱን የላቀ ሚና በመወጣት ላይ የሚገኝ መሆኑን አስረድታለች።

የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን በራሱ ዓይን ተመልክቶ ወደሌሎች በማጋባት ተፅዕኖ መፍጠርም የቻለ ትጉህ ደራሲ መሆኑንም ነው የገለፀችው። ወጣቱ ደራሲ በተባ ብዕሩ እና በራሱ ፍልስፍና ዓለምን ባየው ልክ ሊያመላክተን እድትሆን በሚፈልጋት ጥሩ መልክ ስሎና የራሱን ልዩ አለም ፈጥሮ የማቅረብ ልዩ ክህሎት እንዳለው መስክራለች።

በመድረኩ ላይ ተገኝተው በደራሲው ስራዎች ላይ ዳሰሳዊ ፅሁፍ ያቀረበው ደራሲ ጌታቸው በለጠ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በበኩሉ፤ ደራሲውን በስራዎቹ እንደሚያውቀውና ፅሁፎቹ እጅጉን እንደሚማርኩት የአፃፃፍ ስልቱና የሚያነሳቸው ሀሳቦቹ እንደሚገዝፉበት ገልጿል። ደራሲው ከመፅሀፎቹ በተጨማሪ ጋዜጦች ላይ በሚያጋራቸው የተለያዩ ፅሁፎቹ አገራዊ እይታዎቹ የሚያስደንቁ መሆናቸውን የጠቆመው ደራሲ ጌታቸው በወጣትነት እድሜው እንዲህ የስነ ፅሁፍ ክህሎትና የነጠረ ሀሳብ ማቅረብ መቻሉ የሚገረምበት መሆኑን ገልጿል።

ደራሲው በድርሰት ስራዎቹ ውስጥ በሚስላቸው ገፀ ባህሪያት እና ታሪኮች ቤተሰባዊ ማህበረሰባዊና አገራዊ ጉዳዮች በተለያየ መልክ በማሳየትና በማስተማር የሚታወቅ መሆኑን ገልፆ የራሱ የሆነ የአገላለፅ መንገድ መከተሉም በስነፅሁፉ ረገድ የተሻለ ክህሎት ያለው ለመሆኑ ምስክር መሆኑ ከመፅሀፎቹ እየወሰደ የጠቃቀሳቸው ማስረጃዎችን በማቅረብ አመላክቷል።

ጥበብ በተለይም መጽሀፍት ማህበረሰብን በማነፅ ትውልድን በመቅረፅ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው። በተለየ ምልከታ በተከሸነ መልኩ ጉዳዮች አዋዝቶ በማሳየትና በማስተማር ረገድ ጠቢባን ይህንን አደራ ተረክበው በየዘርፋቸው ማህበረሰባቸውን ያስተምራሉ ያነቃሉ። ደራሲ ዘላለም የሳጥን ወርቅ በመጽሀፎቹ በተለያየ መልኩ ትውልዱን በማስተማርና በማነፅ በትጋት በመስራ ላይ እንደሚገኝም ፅሁፎቹን በመድረክ ላይ አቅርበው አስተያየት በሰጡ የስነ ጽሁፍ ሀያስያን ተገልጿል ።

እኛም በወጣትነት በዘርፉ ስኬታማ ከሆነውና ለብዙ ወጣቶች በትጋቱ አርአያ ይሆን ዘንድ በማሰብ ስራዎቹን የዳሰስንበት ፅሁፍ ለደራሲው ቀጣይ ስኬት በመመኘት ቋጨን። ቸር ያሰማን።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## በአባትና ልጁ ቅን ልቦች የታሰቡ ነፍሶች

ሰላማዊት ውቤ

የዘንድሮ ክረምት ገና ከመግቢያው ጠንከር ያለ ነው። የሚያወርደውን ዶፍ በአዲስ አበባ ከሚገኙ የቀበሌ ቤቶች አብዛኞቹ ሊቋቋሙት አልቻሉም። ቀበሌ ዕድሳት ስለማያደርግላቸውና ነዋሪዎቻቸውም ለማደስ የሚያስችል አቅም ስለሌላቸው አብዛኞቹ በዝናቡ እየፈረሱ ይገኛሉ።

በወረዳ አራት መሳለሚያ እየተባለ የሚጠራው አካባቢ በአንድ ግቢ ውስጥ ከሚገኙ ሰባት የቀበሌ ቤቶች የሶስቱ ዕጣ ፈንታ ይሄ ሆኖ መቆየቱን በቤት ውስጥ የሚኖሩት ሰዎች ይናገራሉ ።

ዕድሜያቸውን በውል ባያውቁትም ጃንሆይ ፋሽሽትን ድል አድርገው ወደ አገራቸው በተመለሱ ሦስተኛ ዓመት ላይ ነው ግንጪ በሚባለው አካባቢ የተወለዱት፤ እናት እልፍነሽ በአሉ ግቢ ውስጥ በሚገኘው የቀበሌ ቤት መኖር ከጀመሩ 35 ዓመታትን አስቆጥረዋል። ወደዚህ ቤት የገቡት መርካቶ አውቶቡስ ተራ አካባቢ ወንዝ ዳር የነበረውን ቤታቸውን ለውጠው ነው ። ሲገቡ ቤቱ በጥሩ ይዞታ ላይ እንደነበረ ያስታውሳሉ ። ከጊዜ ብዛት በማርጀቱ እየፈረሰ መጣ። በተለይ ጣሪያው ብዙ ቦታዎች በመበሳቱ ባለፉት አራት ክረምቶች ቁም ስቅላቸውን ሲያሳያቸው ነው የኖረው። በቤት ውስጥ ያለውን ዕቃ፤ ከጎረቤት በተበደሩት በትላልቅ የልብስ መዘፍዘፊያ በሙሉ በመደቀን ቆመው የሚያድሩበት ጊዜ ብዙ ነው ። እንዳያድሱት አቅም የላቸውም። ባለቤታቸው በዕድሜ ምክንያት ይሰሩበት የነበረውን የግል ጫማ ቤት ሥራ አቁመው ቤት ከዋሉ ብዙ ጊዜያቸው ነው።

ከዚህ በፊት ከወዲያ ወዲህ ተሯሩጣ ምትደጉማቸው አንዲት ሴት ልጅ ብትኖራቸውም ገና በወጣትነቷ ታማ የአልጋ ቁራኛ ከሆነች 30 ዓመቷ ነው። በመሆኑም ጎረቤቶቻቸው ችግራቸውን ለመንግስት አስረድተው በየወሩ በሚሰጣቸው 700 ብር ነው የሚተዳደሩት። ኑሮ ውድ በመሆኑና ብሩ የቤቱን ክራይ ከፍሎ ለቀለብ ስለማይበቃቸው አንዴ ምሳ ሌላ ጊዜ እራት እያሉ ጎረቤቶቻቸው በሚያበሏቸው ይደጉሙታል። ቤታቸውንም ቢሆን በየክረምቱ ሲጠግኑላቸው ነው



አቶ አሳሚን መሐመድ እና አባታቸው አቶ መሐመድ ብርሃን

የቆዩት። ሆኖም ዘንድሮ ዝናቡ ኃይለኛ በመሆኑ እንደፊቱ ሊቋቋመው ባለመቻሉ ሙሉ በሙሉ በዶፉ ፈርሶባቸዋል።

አሁን ላይ ከዚህ በፊት የአካባቢውን አረጋውያንና ኑሯቸው ዝቅተኛ የሆነ የአካባቢውን ነዋሪዎች ቀለብ በመስፈርም ሆነ በገንዘብ ይደጉሙ የነበሩ የአካባቢው ተወላጅ ሙሉ በሙሉ አፍርሰውና አንድ ክፍል የዕቃ ቤት ሁሉ ጨምረው በብሎኬት እየሰሩላቸው እንደሚገኙም ወይዘሮ እልፍነሽ ነግረውናል። እስኪያልቅ ከቅዝቃዜ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ኃይለኛ አስም ስላለባቸው ሁሌ የምትደግፋቸው ጎረቤታቸው መኝታ ቤቷን ለቃላቸው ከነባለቤታቸው እሷ ጋር ነው ያሉት።

በዚሁ ግቢ ከሚገኙት በዝናቡ ምክንያት ከፈረሱ ሦስት የቀበሌ ቤቶች ሁለተኛው የአራሷ የወይዘሮ አይሻ አወል ነው። አይሻ እንደነገረችን አቅፋ እያጠባች ያለችውን የሁለት ወር እርጥብ ልጅ ጨምሮ ስድስት ልጆች አሏት። ቤቱ በላይዋ ላይ በመውደቁ ልጇን የወለደችው ጎረቤት ተጋግዞ አውጥቷት እዛው ላይ ሸራ ወጥሮላት ነው። የወደቀው በተደጋጋሚ ለቀበሌ አመልክታ ባለመታደሱ ነበር። በግሏ እንዳታድሰው ድንችና ሽንኩርት ቸርችራ ነበር የምታድረው፤ አሁን ላይ ደግሞ እሱንም መስራት የማትገችልበት የጀርባ ህመም ከፍተኛ የአጥንት ስብራት ስላጋጠማት ስራውን ትታለች።

አሁን የምትተዳደረው ባሏ ግለሰብ ጋር ጥበቃ እየሰራ በሚያገኘው 800 ብር ነው። ብሩ ገና ሳይመጣ በ15 ቀኑ በሱቅ ዱቤ ነው የሚያልቀው። ደግነቱ አምስቱ ልጆቿ ትምህርት ቤት ስለሚመገቡ ቁርስና ምሳ አታስብም። የኮረና ጊዜግን በጣም ተቸግራ ነበር። እሷ በቤት ውስጥ የሚላስ የሚቀመስ ጠፍቶ ሦስት ቀን ጦሟን ማደሯን ታስታውሳለች። በዚህ ችግሯ ደርሰው ቤቷን በብሎኬት እየገነቡላት የሚገኙትንና በጎነትን ከ102 ዓመቱ የዕድሜ ባለፀጋ አባታቸው ሀጂ መሐመድ ብርሃን የወረሱትን አቶ አላሚን መሐመድን ደጋግማ ታመሰግናለች። ግለሰቡ በደረሳቸው መረጃ መሰረት ሰዎቹ ያሉበትን ሁኔታ ከነልጃቸው መጥተው አይተው የነበሩበትንም ታነሳለች። ደሆችን በመርዳትና ከግቢው ጀርባ ያለውን ትልቁን የቢላል መስጂድ በመገንባት በአካባቢው የልማት ሥራዎችን ሲያከናውኑ የኖሩ ቅኖች መሆናቸውን ትጠቅሳለች።


ሦተኛው የተደረመሰው የቀበሌ ቤት የሶስት ወላጅ አልባ ልጆች ቤት ነው። የቤቱ ትልቅ የምትባለው ወጣት እንደምትለው አባታቸው ከሞተ 16 ዓመት ፤ እናታቸው ከሞተች ደግሞ 10 ዓመት ሆኗታል። እናቷ ስትሞት የ10 ዓመት ልጅ ነበረች። እሷን ጨምሮ ወንድሞቿን ያሳደጓቸው ጎረቤቶች ናቸው ። ዓመት በዓልን የሚያከብሩት የግቢው ሰው ከየኪሱ ገንዘብ አዋጥቶ ከቅርጫ ጀምሮ ለበዓሉ የሚያስፈልጋቸውን አድርጎላቸው ነው። በተለይ የቤዛ አለማየሁ እናት ከልጆቿ እኩል እያበላች እያጠጣች ነው እዚህ ያደረሰቻቸው። እሷ ትምህርቷን እስከ ስምንተኛ ክፍል ወንድሞቿም የተወሰነ ደረጃ እንዲማሩም አድርጋለች። አሁን ላይ እርሷ የጋራዥ ሰራተኞችን ልብስ እያመጣችና አንዳንድ ሥራዎች እየሰራች ወንድሞቿን ብታስተዳድርም የፈረሰውን ቤት ለመሥራት ግን አቅም አልነበራትም። ቤቱ ከመፍረሱም በላይ ከሥር የመፀዳጃ ፍሳሽ ስለሚገባበት ለመኖር ተቸግረው ነበር ።

አሁን ላይ አባታቸውና እሳቸው ደሆችን በመርዳት በጣም የታወቁ ነጋዴ በብሎኬት እየገነቡላቸው በመገኘታቸው ተደስታለች።

አቶ አላሚን መሐመድ ግንባታውን በ150 ሺህ ብር መጀመራቸውን ይናገራሉ። ተወልደው ያደጉት እዛው አካባቢ ነው ።ሰዎቹንም ነዋሪዎች በመሆናቸው ያውቋቸዋል። ኑሯቸው ለቤት ዕድሳት ቀርቶ የእለት ጉርሳቸው አይሸፍንም። ያሉበትን ያዩት ከቀናት በፊት ከ102 ዓመቱ አባታቸው ጋር ጎብኝተዋቸው ነው። ወላጅ አባታቸው ሀጂ መሐመድ ብርሃን ለጉምሩክ፤ለአሜድላና ለተለያዩ ክለቦች ተጫዋች የነበሩ ናቸው። የንግድ ምክርቤትን ከመሰረቱት አንዱ ናቸው። የቢላል መስጂድንም መስርተውና አሰርተዋል።የፈረሱ የደሃ ቤቶችን በመገንባትና ችግርተኞችን ሁሉ ሰብስበው በመርዳት በርካታ የልማት ሥራዎች በመሥራትም ይታወቃሉ። በቅርቡ ሦስቱ የቀበሌ ቤቶች ሙሉ በሙሉ በመፍረሳቸው ነዋሪዎቻቸው በእጅጉ መቸገራቸውን ተመልክተዋል።

በወረዳ 4 የሕብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ኃላፊና የአካባቢው ነዋሪ አቶ ንጉስ አድነው እንደሚሉት እሳቸውም ሆኑ አባታቸው ቅን ልቦች አሏቸው።በብርቱ ደሆችን ያስባሉ።በተለይ አባታቸው እንደ አገር በስፖርቱና በንግዱ ዘርፍ ካበረከቱት አስተዋጽኦ ባሻገር በበጎ ሥራቸው በአካባቢው ይታወቃሉ። ልጃቸውም በጎነትን ከአባታቸው ወርሰዋል። ያሉበትን አይተው እጅግ አዝነው ቤታቸውን አስገንብተውላቸዋል። ሰው ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው በሚል ቢሂል በአካባቢው የፈረሱ የደሃ ቤቶችን ከመገንባት ጀምሮ ፤ቀለብ በመስፈርና ማዕድ በማጋራት እንዲሁም በሚያንቀሳቅሱት ንግድ ለአካባቢው ወጣት የሥራ ዕድል ፈጥረዋል።

# ዓለም አቀፍ




## የዓለምን የዋጋ ግሽበት እያባሰው ያለው የቡድን 7 ሀገራት በሩሲያ ላይ የሚጥሉት ማዕቀብ

ሰሞኑን በጀርመን የተሰበሰቡት የቡድን 7 ሀገራት በሩሲያ ላይ አዲስ ተጨማሪ አዲስ ማዕቀብ ጥለዋል። የዩክሬን ቀውስን ተከትሎ እየተጣሉ ያሉት ማዕቀቦች ወደ ሩሲያ ኢኮኖሚ ምንም ዓይነት የውጭ ካፒታል እንዳይገባ ለመገደብ የተነደፉ መሆናቸውም ይነገራል።

አሁን ይፋ ያረጓቸው ማዕቀቦች መካከል የሩሲያን የወርቅ ምርት ኢላማ ያደረገ ነው። ሲጂቲኤን በድረገፁ ያወጣው የዓለም ፖለቲካ ተመራማሪው ፍሬዲ ሬዲን ፅሁፍ "ይህ አዲስ ማዕቀብ ለውጥ ያመጣ ይሆን?" ሲሉ ይጠይቃሉ። ፀሃፊው በምዕራባውያኑ ሀገራት የተጣሉት ማዕቀቦች የዓለምን የዋጋ ግሽበት በማማባስ ራሳቸውን ማእቀብ የጣሉ ሀገራትን ሳይቀር በአስከፊ የኢኮኖሚ ጫና ውስጥ እንደከተታቸው ያስረዳል።

የጀርመኑ መራሂ መንግሥት ኦላፍ ሾልዝ የተጣሉት ማዕቀቦች እንዲነኩ ከሚታሰቡት ሀገራት ይልቅ ማእቀብ በጣሉት ሀገራት ላይ ያመጣው አሉታዊ ተፅዕኖ የበለጠ ሊሆን አይግባም ሲሉ ተደምጠዋል። የቡድን ሰባት ሀገራት እና የአውሮፓ ህብረት አባላት የሩስያ ወርቅ ግዢን በመጋቢት ወር አቅመዋል። በመሆኑም የወርቅ ዋጋ ወደ 1 ሺህ 856.86 የአሜሪካ ዶላር በማሻቀብ የዋጋ ግሽበትን አስከትሏል።

በፈረንጆቹ 2021 የሩሲያ የወርቅ ወጪ ንግድ ከ15 ቢሊዮን ዶላር በላይ ደርሷል ተብሎ የሚገመት ሲሆን፥ ነገር ግን የሀገሪቱ የወርቅ ምርት ሽያጭ ከሰኞው ማዕቀብ በፊት አሽቆልቁሎ እንደነበር ያትታሉ። የአሁኑ የቡድን 7 አገራቱ አዲስ ማእቀብ በሩሲያ ላይ ለያዙት አቋም ተምሳሌታዊ መልክ ከመስጠት ያለፈ ሌላ ትርጉም የለውም ባይ ናቸው።

እጅጉን በኢኮኖሚ ተሳስራ በምትኖረው ዓለም በሩሲያ ላይ እየተጣሉ ያሉት ማእቀቦች ሁለቱንም ወገኖች ዋጋ እያስከፈለ መሆኑን ያስረዳሉ። ዩናይትድ ስቴትስ በሩሲያ ላይ በጣለቻቸው ማእቀቦች ምክንያት በሀገሯ የከፋ የኑሮ ውድነትን እንድታስተናግድ አድርጓታል።

ዩክሬን በፊናዋ ይህ የኢኮኖሚ ማዕቀቦች ፈጣን ለውጥ አምጥተው ከገጠማት ጦርነት በፍጥነት እንድትወጣ እንደማያደርጋት በመገንዘብ ምዕራባውያኑን እየተማፀነች ያለችው ወታደራዊ መፍትሄ ላይ እንዲያተኩሩ ነው። ይልቁንም የቡድን 7 ሀገራቱም ሆኑ ሌሎቹ ሀገራት ወደ ሰላም መንገድ በሚወስድ ተግባራዊ እርምጃ ላይ ቢያተኩሩ ለሁሉም እንደሚያዋጣ ተመራማሪው መምከራቸውን ኤፍቢሲ ዘግቧል።

## ሲሪላንካ ወሳኝ ላልሆኑ አገልግሎቶች ነዳጅ መሸጥ አቆመች

ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ እጅግ የከፋ የኢኮኖሚ ቀውስ እያጋጠማት የምትገኘው ሲሪላንካ ወሳኝ ላልሆኑ ተሽከርካሪዎች ነዳጅ መሸጥን አቁማለች። በሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት ለህክምና አገልግሎት እና ምግብ ለማጓጓዝ የሚያገለግሉ ተሽከርካሪዎች፣ አውቶቡሶች፣ ባቡሮች እና ተሽከርካሪዎች ብቻ ነዳጅ እንዲሞሉ ተፈቅዶላቸዋል።



መንግሥት በከተሞች የሚገኙ ትምህርት ቤቶች እንዲዘጉ ያደረገ ሲሆን፣ የአገሪቱ 22 ሚሊዮን ነዋሪዎች ከቤት እንዲሠሩ በባለሥልጣናት ተነግሯቸዋል። የደቡብ እስያዋ አገር እንደ ነዳጅ እና ምግብ ያሉ ከውጭ ለሚገቡ ምርቶች ክፍያ ለመፈጸም የሚያስችላትን ገንዘብ ለማግኘት እየተነጋገረች ነው።

"በ1970ዎቹ የነዳጅ ቀውስ ተፈጥሮ በአሜሪካ እና በአውሮፓ ያለውን ፍላጎት ለመቀነስ የተሽከርካሪዎች የፍጥነት ገደብ እና የኮታ አቅርቦት ከተዋወቀ ወዲህ ስሪላንካ ለተራው ሰው የነዳጅ ሽያጭን በማስቆም ከባድ እርምጃ የወሰደች የመጀመሪያዋ አገር ሆናለች" ሲሉ በኢንቨስቴክ የጋዝና ነዳጅ ምርምር ኃላፊው ናታን ፓይፐር ለቢቢሲ ተናግረዋል።

እገዳው በሲሪላንካ ያለውን ከፍተኛ የነዳጅ ዋጋ መጨመር እና የውጭ ምንዛሪ ክምችት ውስን መሆኑን በግልጽ አሳይቷል። ብዙዎቹ የደሴቲቱ ነዋሪዎች ያለ ነዳጅ ኑሯቸውን እንዴት እንደሚገፉ ግራ ተጋብተዋል። ለወራት በስሪላንካ በሚገኙ የነዳጅ ማደያዎች ረዣዥም ሰልፎች ይታዩ ነበር።

በኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ ከተከሰተበት የኢኮኖሚ ቀውስ ሌላ የነዳጅ ዋጋ መጨመር እና የታክስ ቅነሳ መደረጋቸው ተደማምረው ስሪላንካ አስፈላጊ ዕቃዎችን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስችላትን በቂ የውጭ ምንዛሪ እንድታጣ ምክንያት ሆኗል።

ከፍተኛ የነዳጅ፣ የምግብ እና የመድኃኒት እጥረት የአገሪቱን የኑሮ ውድነት እንዲንር አድርጎታል። ብዙዎች ገቢያቸውን ከግል ሞተር ሳይክሎቻቸው ያገኛሉ። ሰኞ ዕለት የአገሪቱ መንግሥት እስከ ሐምሌ 10 ድረስ የግል ተሽከርካሪዎች ቤንዚን እና ናፍታ እንዳይገዙ እንደሚከለክል ተናግሯል።

የአገሪቱ ካቢኔ ቃል አቀባይ ባንዱላ ጉኔዋርዴና በበኩላቸው ስሪላንካ "በታሪኳ እንደዚህ ያለ ከባድ የኢኮኖሚ ቀውስ ገጥሟት አያውቅም" ብለዋል። በገንዘብ ችግር የተሸበሸበችው አገር ርካሽ የነዳጅ አቅርቦት ለማግኘት ባለሥልጣናትን ወደ ነዳጅ አምራቾቹ ሩሲያ እና ኳታር ልካለች።

አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ራኒል ዊክሬሜሲንጌ በዚህ ወር መጀመሪያ ላይ እንደገለጹት እንደ ምግብ፣ ነዳጅ እና ማዳበሪያ ላሉ አስፈላጊ ዕቃዎች ለመክፈል አገሪቱ በሚቀጥሉት ስድስት ወራት ቢያንስ 5 ቢሊዮን ዶላር ያስፈልጋታል።

የምግብ እጥረት ሊከሰት ይችላል በሚልም ባለፉት ሳምንታት ሚኒስትሮች ገበሬዎች ብዙ ሩዝ እንዲያመርቱ ጠይቀዋል። መንግሥት በሲሪላንካ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ከሚያስገኙት አንዱ የሆነው የቱሪስት ዘርፍ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ መጎዳቱን ለቀውሱ ተጠያቂ አድርጓል። ብዙ ባለሙያዎች ግን የመልካም አስተዳደር እጦት ለኢኮኖሚው ውድቀት ዋነኛው መንስኤ መሆኑን የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
BAKKALCHO
www.press.et
Ethiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ስፖርት
ሐሙስ



ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት
ነው!

# የዓለም ቻምፒዮናው ለሶስተኛ ድሉ እየተሰናዳ ነው

**ብርሃን ፈይሳ**

በአሜሪካዋ ዩጂን ግዛት ኦሪጎን ከተማ የሚካሄደው 18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የሁለት ሳምንታት ዕድሜ ብቻ ቀርተውታል። የውድድሩ አዘጋጅ ከተማ ኦሪጎንም አትሌቶችን ለመቀበል እየተሰናዳች ትገኛለች። የአትሌቲክሱ ዓለም ምርጥ አትሌቶች ብቃታቸውን ለማስመስከር እንዲሁም የሃገራቸውን ስም ለማስጠራትም ዝግጅታቸውን በማጠቃለል ላይ ናቸው። በስፖርቱ ስመጥር ከሆኑት ሃገራት መካከል የምትመደበው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድንም በዝግጅት ላይ ይገኛል።

ከአጠቃላይ ቡድኑ ውስጥም በርካታ አትሌቶች የሚካፈሉበት የ5ሺ ሜትር ወንዶች ምድብ ነው። ለተፎካካሪዎች አስፈሪ በሆነው በዚህ ቡድን የዓለም ቻምፒዮናውን ሙክታር እድሪስን ጨምሮ ከእነተጠባባቂው አምስት አትሌቶች ተይዘዋል። ሙክታር በለንደኑ የዓለም ቻምፒዮና ባልተጠበቀ ሁኔታ የርቀቱን የበላይነትን ከኢትዮጵያውያን እጅ በመንጠቅ የግሉ ያደረገውን እንግሊዛዊ አትሌት በመርታት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የስኬት ጉዞው እንዲደመደም በማድረጉ ይታወሳል። በትውልድ ሶማሊያዊ በዜግነት ደግሞ እንግሊዛዊ የሆነው ሞሃመድ ፋራህ ለሶስት ዓመታት የ5ሺ እና 10ሺ ሜትር ድሎችን ለብቻው በመጠቅለል የዓለም ቁንጮ ሆኖ ነበር። ለንደን ላይ ግን ከፍተኛ ግምት ያልተሰጠው ሙክታር በአስደናቂ አጨራረስ የወርቅ ሜዳልያውን ርቆ ከሄደበት አስመልሶ የሀገሩን ስም ዳግም አስጠርቷል።

የእንግሊዛውያን መመኪያ የሆነው ሞ ፋራህ በወቅቱ መቀደሙን ለማመን የተቸገረ ከመሆኑም ባለፈ የውድድር ሕይወቱም ላይ ለውጥ ያስከተለ ሽንፈት ነበር በሙክታር



አትሌቱ በኦሪገን የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና በ5ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ እንደሚያጠልቅ ይጠበቃል፤

የደረሰበት። ቻምፒዮናው ሙክታርም የርቀቱን ንግስና እአአ በ2019ኙ የኳታር ዓለም ቻምፒዮናም በድጋሚ በመቀዳጀት የበላይነቱን አስጠብቋል። በዓለም አትሌቲክስ ጋባዥነት በኦሪጎን ቻምፒዮና በቀጥታ ተካፋይ የሆነውና ቡድኑን የሚመራው አትሌቱ ጥቂት ሳምንታት ለቀሩት ውድድር እየተደረገ ስላለው ዝግጅት ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ቆይታ አድርጓል።

ዝግጅቱን አስመልክቶ «እንደሌላው ጊዜ የሀገራችንን ባንዲራ ዝቅ ላለማድረግ በትጋት እየሰራን ነው» ብሏል። በቡድኑ ጥሩ ብቃት ላይ ያሉ አትሌቶች መኖራቸውን የሚያነሳው አትሌቱ እርሱ ግን ከነበረበት ጉዳት ሙሉ ለሙሉ ባያገግምም አብሯቸው በመሆን ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት ያደርጋል። መቀመጫቸውን በኔክሰስ ሆቴል ያደረጉት የቡድኑ አባላት በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ፣ በቃሊቲ፣ እንጦጦ እንዲሁም ሱሉልታ አካባቢ እየቀያየሩ ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ቡድኑ እንደ ሌላው ሀገር በሳይንሳዊ ዘዴ ሳይሆን በከፍተኛ ስፍራዎች ላይ ልምምዱን የሚያደርግ ሲሆን፤ አሁን በኢትዮጵያ ያለው ወቅት ክረምት በመሆኑ በተወሰነ መልክ ዝግጅቱን ከባድ አድርጎባቸዋል። ነገር ግን አብዛኛው የዝግጅት ጊዜ እየተጠናቀቀና ወደ ውድድር እየተንደረደሩ በመሆኑ ራሳቸውን ከሁኔታዎች ጋር በማጣጣም እየሰሩ መሆኑንም ያስረዳል።

የለንደን እና የኳታር ቻምፒዮን ዘንድሮ ደግሞ በኦሪጎን ሶስተኛውን ተከታታይ ስኬት በማስመዝገብ ታሪካዊ አትሌት ለመሆን እየተሰናዳ ይገኛል። ሶስቱ ተከታታይ ውድድሮች በአትሌቱ ላይ ያላቸው መልክ ምን ይመስላል በሚለው ላይ የሚከተለውን አስተያየት ሰጥቷል። ሞ ፋራህን ባሸነፈበት የለንደኑ ዓለም ቻምፒዮና በመልካም ጤንነት ላይ ሆኖ ነበር የተሳተፈው። በኳታሩ ቻምፒዮና ላይ ተጋባዥ ቢሆንም ጉዳት ላይ ሆኖ በመሮጥ ያልተጠበቀ አሸናፊነት በማስመዝገብ ነበር በድጋሚ የወርቅ ሜዳሊያውን ያጠለቀው። ዘንድሮም በተመሳሳይ ህመም ቢገጥመውም ከቡድን አጋሮቹ ጋር በመሆን ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ እንደሚሮጥ ገልጿል።

በዚህ ርቀት ከእርሱ ጋር የሚሮጡትና በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የተዘጋጀውን ሚኒማ በማሟላት የተመረጡት አትሌቶች በጥሩ ቁመና ላይ የሚገኙ መሆናቸውን አትሌቱ ያስረግጣል። አትሌቶቹ በዓመቱ በነበሩ ውድድሮች ላይ ሲያሳዩ የቆዩት ብቃት መልካም የሚባል ሲሆን፤ እርሱ ያለውን የተሻለ ልምድ በማካፈል ዝግጅቱ እየተከናወነ ይገኛል። በውድድሩ ላይም የኢትዮጵያ ቡድን አራት አትሌቶችን ይዞ መቅረቡ በራሱ ለሌሎች ተፎካካሪዎችን ከማድከም አንጻር የራሱን ሚና ከመጫወቱም በላይ የቡድን ስራ ለመስራትም ይመቻል። በመሆኑም በርቀቱ የተለመደው ወርቅ ይታጣል የሚል ግምት እንደሌለው አመላክቷል።

EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# አገልግሎት አሰጣጥን ያቀላጠፈውና ሙስናን በመከላከል ረገድ አቅም የፈጠረው ዲጂታላይዝድ አሰራር

**ታምራት ተስፋዬ**

የኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ባለሥልጣን አገር ውስጥ የሚመረቱና ከውጭ የሚገቡ ምግብ መድሃኒትና የህክምና መሳሪያዎችን ጥራት፣ ደህንነት፣ ፈዋሽነት ያረጋግጣል። በዚህም ሕብረተሰቡን ጥራት ፣ ደህንነትን ብቃቱ ካልተጠበቀ ምግብና መድሃኒት ይከላከላል።

ይህን ሃላፊነቱን ለመወጣትም በዋና መስሪያ ቤትም ሆነ በቅርንጫፎች ጣቢያዎቹ የተደራጁ የተለያዩ የቁጥጥር ክፍሎች አሉት። እንደ ባለሥልጣን መስሪያ ቤት በአገሪቱ የተለያዩ ክልሎች ቅርንጫፎች አሉት። የማእከላዊ ቅርንጫፍም ከእነዚህ አንዱ ነው።

በማእከላዊ ቅርንጫፍ በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ አምስት መግቢያ መውጫዎች አሉ። በኢትዮጵያ አየር መንገድ ካርጎና በመንገደኞች አገልግሎት ሁለት ቅርንጫፍ ቢሮ አለ። ቃሊቲ ወደብና ተርሚናል፣ በአዳማ እንዲሁም በሞጆ ወደብና ተርሚናል ቢሮዎች አሉት።

አቶ አያልሰው መለሰ በኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ባለሥልጣን የማእከላዊ ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሃላፊ ናቸው። በእነዚህ መግቢያ መውጫ ቁጥጥር ጣቢያዎች መድሃኒትና የህክምና መሳሪያዎች ደህንነት፣ ፈዋሽነት፣ ጥራት በማረጋገጥ ረገድ ምን እንደሚከናወንና በተለይ ተቋሙ አገልግሎቱን ዲጂታላይዝ ማድረጉ ምን ለውጦችን መመልከት ተቻለ የሚል ጥያቄ በማንሳት ቆይታ አድርገናል።

አቶ አያልሰው እንደሚገልጹትም፣ ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ቁጥጥር የሚያደርግባቸው ምርቶች መግቢያ መውጫዎች ላይ ሲደርሱ የጥራት፣ የደህንነት፣ ፈዋሽነት እና ብቃት ደረጃቸው ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል። በመውጫ መግቢያዎች በኩል ምርቶች ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ሲገቡም ሆነ ከአገር ወደ ውጭ ሲወጡ መሟላት ያለባቸው ከደህንነት



አቶ አያልሰው መለሰ

ከጥራት፣ ከብቃት አንጻር የተለያዩ መስፈርቶች አሉ። ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ በተሰጠው ሥልጣንና ሃላፊነት መሰረት የቁጥጥር ስራ ይሰራል።

በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ከጥቅም ጋር በተገናኘ ባለሙያዎችን ከመደለል፣ ከማባበል ጋር የተገናኙ ችግሮች ይኖራሉ። እነዚህ አይነት ችግሮችን ለማስቀረት መሰራት ያለባቸው ጉዳዮች አሉ። ቀዳሚው ግልጸኝነትን መፍጠር ነው። ሁለተኛ ተጠያቂነትን ማስፈን ነው። ተቋሙ ለእነዚህ ነገሮች ትኩረት በማድረግ የተለያዩ ስራዎች ሰርቷል። አንደኛውና ትልቁ ስራም ስራዎችን በሙሉ ዲጂታላይዝ ማድረግ ነው።

በአሁኑ ወቅትም መግቢያ መውጫ ጣቢያዎች ላይ ላይ በወረቀት የሚሰራ ስራ የለም። አገልግሎቶች በሙሉ ዲጂታላይዝ ተደርገዋል። ተቋሙ አገልግሎቱን ዲጂታላይዝ በማድረጉ ሁሉም ባለሙያዎች የሚሰራት ስራ በሃላፊዎች ይታያል። አንድ ማመልከቻ የሚገባበትና ቁጥጥር ተደርጎበት ተፈትሾ የሚወጣበት ሰአት ይታወቃል። አገልግሎትና የቁጥጥር ስራው በምን መንገድ ተከናወነ፣ በምን መልኩ ምላሽ ተሰጠው፣ በሂደቱ የትኞቹ ባለሙያዎች ተሳትፈዋል የሚለው ይታወቃል። አገልግሎት ፈላጊም በአካል መቅረብ ሳይጠበቅበት ካለበት ሆኖ አገልግሎቱን መከታታል የሚችልበት አቅም ፈጥሯል። የተለያየ ቁጥጥር፣ ፈቃድ እና ሌሎችንም አገልግሎቶች የሚከውኑ ክፍሎች ስራቸውን ተናበው እንዲሰሩ አስችሏል። ይህም አገልግሎት አሰጣጡን አቀላጥፎታል።

ተቋሙ መሰል ዘመናዊ የአሰራር ሥርዓቶች መዘርጋቱም ዘርፈ ብዙ ፋይዳ አለው። በዋነኝነት የግልጽኝነትና የተጠያቂት አሰራርን በማስፈን በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ቀደም ሲል ይስተዋሉ የነበሩ ችግሮችን ፈር ለማስያዝ እያገዘ ይገኛል። ሕብረተሰቡ የተመዘገቡም ሆነ መወገድ ያለባቸውና የጤና እክል የሚያመጡ ምርቶችን እንዳይጠቀም በማስገንዘብ ረገድ በርካቶችን ለመድረስ አስችሏል። ጥቆማ ካለም እንዲሰጥ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል።

ተጠያቂነትን እንዲሰፍንና የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ የለም በሚባል ደረጃ እንዲጠፋ ከፍተኛ አቅም ፈጥሯል። ተቋሙ በዚህ መልክ በተቻለ መጠን አሰራሩን ግልፅ ለማድረግና የባለሙያዎችን ተጠያቂነት ከማስፈን አንጻር ብዙ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል።

ይህ ማለት ግን ችግሮች የሉም ማለትም አይደለም። በስራ ሂደት ሙስናናን ጨምሮ የተለያዩ ችግሮች ሊስተዋሉ ይችላሉ። በመሰል ተግባራት ውስጥ ተሳትፈው ያገኘናቸውን ባለሙያዎች በተቋሙ የሥነ ምግባር ደንብ መሰረት ተጠያቂ አድርገናል። እያደረገንም እንገኛለን።

ተቋሙ አዲስ መዋቅር ይፋ አድርጋል። አንደኛው ትኩረት ቅርንጫፍ ጣቢያዎች ማስፋት ነው። መጨመር ነው። በአንዳንድ ክልሎች ላይ ከአንድ በላይ ተጨማሪ ቅርንጫፍ ጣቢያዎች እንዲኖሩን ይደረጋል። እነዚህ ቅርንጫፍ ጣቢያዎችም በብቁ ባለሙያዎች ሆነ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚደራጁ ይሆናል።

ማዘመን ሲባል ከቁጥጥር ጋር የሚዛመድ ነው። ቁጥጥር ሲባል ጥራትና ደህንነትን ማስጠበቅን ይጠይቃል። አፈታተሻችንን ማዘመንን ይመለከታል። ይሁንና ዘመናዊ አሰራርን መተግበር ቢቻልም ሕገ ወጥ ተግባር የተሰማሩ አካላት ሁልጊዜም ስልትና አካሄዳቸውን ይለዋውጣሉ።

ቁጥጥር ውስብስብ ስራ ነው። አንድ ተቋም ብቻውን የሚሰራው አይደለም። የተለያዩ ባለድርሻ አካላት እኩል ተስትፎ ይጠይቃል። ይህ ባለመሆኑና በተሳትፎ ወጣ ገባ ማለት ምክንያትም የሚያመልጡ ምርቶች ይኖራሉ። ከጥቅም ጋር በተገናኘም ምርቶች ገበያ ላይ የሚገኙበት አግባብ ሊኖር ይችላል።

ይሁንና በአብዛኛው ምርቶች አምልጠው ገበያ ላይ ሊገኙ የሚችሉት በሕገወጥ መልኩ ወደ አገር የሚገቡ ሲሆን ነው። በህጋዊ መንገድ የሚገቡት የተመዘገበ መረጃ ያላቸው እንደመሆኑ በቀላሉ ለመቆጣጠርና ችግሮችን ለማስተካከል ያስችላል።

ይህ ማለት ችግሮች የሉም ማለትም አይደለም። መቶ በመቶ የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቷል የሚል እምነት የለንም። እንደ ተቋም ብዙ መስራት አለብን ብለን እናምንለን። ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት በተለይም መውጫ መግቢያ አካባቢዎች ላይ ቁጥጥርን ይበልጥ ማጠናከር የግድ ይላል።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482
http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/